# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችትና ሥርጭት አፈጻጸም ላይ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት








ታህሳስ 2006 ዓ.ም

1.መግቢያ ........................................................................................................................................ 1
2. የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፋይናንስ ምንጭ ................................................................ 4
3. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት ............................................................. 4
4. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት ................ 5
5. በግብርና ሚ/ር የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት …. .......................................... 5
6. የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት … ......................................................................... 6
የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description) ............................................................................... 8
7 የኦዲቱ ዓላማ ፡- ............................................................................................................................ 9
8. የኦዲት አካባቢ .............................................................................................................................. 9
9. የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-.................................................................................................. 9
10. የኦዲት መመዘኛ መስፈርት…………………………………………………………………...10
11. የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡- ................................................................................................................. 11
12. የምርት ማሳደጊያዎች በጥራት፣ በወቅቱና በዝቅተኛ ዋጋ ለአርሶ አደሩ መቅረቡን በተመለከተ……………………………………………………………………………..12
15. በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ……………14
17. ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ…………………………………………………………………………..........15
18. የምርት ማሳደጊያዎች መጠናቸውን ጠብቀው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ስለሚደረገው ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ……………………………………………………………………….17
19. የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ፣ ሥርጭት እና ክምችት መረጃ አያያዝን በተመለከተ……………18
20. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች የሚቀመጡበትን ሥርዓት በተመለከተ……………………………………………………………………………..20
21. የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘን አያያዝ፣ ጥራት እና የመገልገያ መሳሪያዎችን በተመለከተ…………………………………………………………………………….21
22. የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚው ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ እና ለብክነት የተጋለጡ የምርት ማሳደገያዎችን በተመለከተ……………………………………………………………………..25
23. በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የሽያጭ ማዕከላት የሚያካሂዱዋቸውን የሽያጭና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በተመለከተ……………….. ………………………………………………………………27
24. የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭትና ክምችት አፈጻጸም ሪፖርትን በተመለከተ……28

መግቢያ........1
2. የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፋይናንስ ምንጭ ........4
3. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት........4
4. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት ........5
5. በግብርና ሚ/ር የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት …. ........5
6. የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት … ........6
የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description)........8
7 የኦዲቱ ዓላማ ፡-........9
8. የኦዲት አካባቢ........9
9. የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-........9
10. የኦዲት መመዘኛ
መስፈርት........10
11. የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡- ........11
12. የምርት ማሳደጊያዎች በጥራት፣ በወቅቱና በዝቅተኛ ዋጋ ለአርሶ አደሩ መቅረቡን
በተመለከተ........1
2
15. በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ........14
17. ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን
በተመለከተ........
15
18. የምርት ማሳደጊያዎች መጠናቸውን ጠብቀው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ሰለሚደረገው ቁጥጥርና
ክትትልን በተመለከተ........17
19. የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ፣ ሥርጭት እና ክምችት መረጃ አያያዝን በተመለከተ........18
20. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች የሚቀመጡበትን ሥርዓት
በተመለከተ........2
0
21. የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘን አያያዝ፣ ጥራት እና የመገልገያ መሳሪያዎችን
በተመለከተ........21

22. የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚው ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ እና ለብክነት የተጋለጡ የምርት ማሳደገያዎችን በተመለከተ........................................................................................25

23. በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የሽያጭ ማዕከላት የሚያካሂዱዋቸውን የሽያጭና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በተመለከተ................... ..................................................................27

24. የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭትና ክምችት አፈጻጸም ሪፖርትን በተመለከተ......28

25. የምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ...........................................................................................................29

26. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች በስርጭት አውታሮች፣ በአከባቢ እና በገበያ ሁኔታ የሚለዩ መሆናቸውን በተመለከተ......................................................................................30

27. የምርት ማሳደጊያዎችን ማስተዋወቅ እና የሽያጭ አውታሮችን ማስፋፋትን በተመለከተ...............................................................................................31

28. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዱቤ ሽያጭን በተመለከተ............................................33

29. ለሚሸጡ የምርት ማሳደጊያዎች የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ብዛት መመዘኛ ደረጃ መዘጋጀቱን በተመለከተ..........................................................................................34

30. ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች ትኩረት መስጠትን በተመለከተ....................................35

31. የምርት ማሳደጊያዎች እጅ በእጅ ሽያጭ ባንክ ገቢ መደረጉን በተመለከተ........................36

32. የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችት እና ስርጭት በቅንጅት መፈጸሙን በተመለከተ...............................................................................................37

33, የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የሚያጓጉዙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሸከርካሪዎችን በተመለከተ.............................................................................38

34. የመደምደሚያ ሃሳቦች..........................................................................................39

35. የማሻሻያ ሃሳቦች...............................................................................................44

36. አባሪ 1፡- የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች.....................................................................48

37. አባሪ 2፡-በኦሮሚያ እና አማራ ክልል መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ሥር የሚገኙ አርሶ አደሮች ጥያቄ እና መልሳቸው የተጠናቀረ.........................................................................5
4

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በአገራችን የግብርና አቅርቦት፣ ሥርጭትና ክትትል ሥራ የተጀመረው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1959 ዓ.ም ሲሆን የማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት ከመንሻው ጀምሮ በተለያዩ መ/ቤቶች ይሠራ እንደነበረና ብዙ ሂደቶችን ያለፈ መሆኑን ለማሳየት በሚከተለው ሁኔታዎች ቀርበዋል፤ ከ1959-1961 ዓ.ም. በዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) አማካይነት፣ ከ1965-1966 ዓ.ም. በእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ ሥር እራሱን ችሎ እንዲሠራ የተቋቋመው የግብርና ግብአት ግብይት አገልግሎት (Agricultural Input & Marketing Service) ፣ ከ1959-1966 ዓ.ም በመንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ከ1967 ዓ.ም. እስከ 1969 ዓ.ም ባለው ጊዜ የግብርና ግብዓት ገበያ አገልግሎት (AIMS) እና ከ1970 -1976 ዓ.ም የግብርና ሰብል ገበያ ድርጅት (AMC) ፣ከ1977- 1984 ዓ.ም በግብርና ሚኒስቴር ሥር የግብርና ግብዓቶች አቅራቢ ኮርፖሬሽን (AISCO) መሆኑን የጽሑፍ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ የማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት በቀደምት ዓመታት በማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት ተከስተው የነበሩ ችግሮችን ከግንዛቤ በማስገባት የአገሪቱን የማዳበሪያ ገበያ በነፃ ውድድር ላይ የተመሠረተ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚደረገውን ብሔራዊ ጥረት ለማገዝ በ1985 ዓ.ም. የማዳበሪያ ፖሊሲ ወጥቷል፡፡ ፖሊሲውን ለመተግበር በተወሰዱ እርምጃዎች ለረዥም ዓመታት በአንድ የመንግሥት ድርጅት ብቻ ተይዞ የነበረው የማዳበሪያ ንግድ ሥራ ለሌሎች ባለሀብቶች ክፍት በመደረጉ በጊዜው 14 ድርድቶች 1 የመንግሥት፣ 2 የግልና 11 የሕብረት ሥራ ዩኒየኖች በማዳበሪያ ንግድ ሥራ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

2. በአገራችን የማዳበሪያ አጠቃቀም በማሳደግ በመንግሥትና በሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ የቆዩ ቢሆንም አገራችን በዓለም ዝቅተኛ የማዳበሪያ ተጠቃሚ ከሚባሉት አገሮች ተርታ አልወጣችም፡፡ እ.ኤ.አ. በመጋቢት 2002

በተዘጋጀው የግብርና ግብዓት ፕሮጀክት ሰነድ ላይ እንደተመለከተው የአገራችን አማካይ የማዳበሪያ አጠቃቀም በእርሻ በሚውል መሬት ላይ በሄክታር 25 ኪሎ ግራም ብቻ ነው፡፡

3. በዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት የ1990 ዓመታዊ የማዳበሪያ ሪፖርት አጠቃቀም ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው ግብጽ በሄክታር 360 ኪሎ ግራም እና ዚምባቡዌ በሄክታር 56 ኪሎ ግራም መሆኑ ተገልጿል፡፡ ከእነዚህ አጋራት ጋር ሲነፃፀር የአገራችን የማዳበሪያ አጠቃቀም እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ ይታያል፡፡ በመሆኑም የማዳበሪያ አጠቃቀማችንን ለማሳደግ ብዙ መሰራት እንዳለበት ከሚመለከተው አካል እንደሚጠበቅ ያሳያል፡፡

4. በመሆኑም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ምርት እና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት የግብርና ግብዓቶችን ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ በመግዛት ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ የሚገኝ በመንግሥት የተቋቋመ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እና በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 174/1986 በተቋቋመበት ዓላማ መሠረት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን፤ የአፈር ማዳበሪያዎች (ዳፕ፣ ዩሪያ...)፣ የአበባ ማዳበሪያዎች (ፈሳሽና አንኳር)፣ የእርሻ ኬሚካሎች (ፀረ-ነፍሳት፣ ፀረ-አረም፣ፀረ-ሰብል በሽታ፣ የአይጥ መርዝ)፣ የመርጫ መሣሪያ፣ የተለያዩ የጓሮ አትክልት ዘሮች፣ የእንስሳት መድኃኒት፣ የላብራቶሪ መገልገያ መሳሪያዎች፣ አነስተኛ የእጅና የእርሻ መሣሪያዎችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፣ ዋጋቸው እንዳይንር የገበያ መረጋጋት መፍጠር እና ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ ሲሆኑ ድርጅቱ ለምርት ማሳደጊያዎች መግዣና ለሥራ ማስኬጃ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መርቸንዳይዚንግና የኦቨርድራፍት ብድር አገልግሎት ያገኛል፡፡

5. በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተስፋፋ የመጣውን የአበባ ምርት ለማገዝ ድርጅቱ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የአበባ ማዳበሪያ እያስመጣ ለተጠቃሚዎች እያቀረበ ቢሆንም በመስኩ ከፍተኛ ሥራ የሚጠበቅበት እንዲሁም በዕድገትና

ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መንግሥት በግብርና ዘርፉ በኩል ያስቀመጠውን ግብ ለማሳካት እንዲቻል ለግብርና ዘርፉ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች በበቂና አስተማማኝ መልኩ በማቅረብ ጉልህ ሚና መጫወት ያለበት ድርጅት ነው፡፡

6. የድርጅቱን የገበያ ድርሻ አስመልክቶ ብቸኛ አቅራቢ እስከነበረበት 1984 ዓ.ም ድረስ በግዥም ሆነ በሽያጭ መቶ በመቶ የገበያ ደርሻ የነበረው ሲሆን ከዚያ ቦኋላ ባሉት ዓመታት ግን በነፃው ገበያ መርህ መሠረት ሌሎች አቅራቢዎች ወደ ገበያው በመግባታቸው የገበያው ድርሻ ሊቀንስ ችሏል፡፡ ከ1994- 1997 ዓ.ም ባለው 4 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የድርጅቱ የማዳበሪያ ሽያጭ ከአገር አቀፍ ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በአማካይ የ62.5 በመቶ የገበያ ድርሻ እንደነበረው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በ1998 ዓ.ም የ26%፣ በ1999 ዓ.ም 36%፣ በ2000 ዓ.ም 25% እና በ2001 ዓ.ም 25 በመቶ የገበያ ድርሻ እንደነበረው ታውቋል፡፡ በማዳበሪያ ግዥ ረገድም ድርጅቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ1994- 1997 በጀት ዓመታት ድረስ በአማካይ 58% የግዥ ድርሻ ነበረው፡፡ ድርጅቱ በ1998 ዓ.ም 13% የግዥ ድርሻ የነበረው ሲሆን በ1999 ዓ.ም 44% የግዥ ድርሻ በ2000 በጀት ዓመት 23 በመቶ የግዥ ድርሻ እንደነበረው መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

7. ድርጅቱ ከሚያቀርበው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዋናው የአፈር ማዳበሪያ /DAP and UREA/ ሲሆን እስከ 95% የሚሆነውን የድርጅቱን ሽያጭ የሚይዝ ነው፡፡ ከአጠቃላይ የአፈር ማዳበሪያዎች ሽያጭ ውስጥ 80% የሚሆነው ለአርሶ አደሩ፣ የህብረት ሥራ ማህበራት፣ ህብረት ሥራ ዩኒየኖች የሚከናወን ሽያጭ ሲሆን፣ ቀሪው 20% ደግሞ ለመንግሥትና የግል እርሻዎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የሚከናወን ሽያጭ ነው፡፡

8. ቀደም ሲል ኦሮሚያ፣ አማራ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ትግራይ ከፍተኛ የማዳበሪያ ተጠቃሚ ክልሎች ሲሆኑ ድርጅቱም በስፋት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርግባቸው ክልሎች ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የክልሎች ገበያ በአብዛኛው በዩኒየኖች የተያዘ በመሆኑ ከአማራና በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ከትግራይ ክልል በስተቀር በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች የድርጅቱ የገበያ ድርሻ የለም ወደሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ይታያል፡፡ ዝቅተኛ ተጠቃሚ በሆኑት በሌሎች ክልሎች

ያለው የሸያጭ አውታር የተወሰነና ያልዳበረ ሲሆን ለማዳበር ያላሰለሰ ጥረትን ይጠይቃል፡፡

## የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፋይናንስ ምንጭ

9. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፋይናንሰ ምንጭ ለሥራ ማስኬጃ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከባንክ በኦቨርድራፍት ብድር ጠይቆ ሥራ ላይ እንዲውል የሚያደርግ ሲሆን፣ የግብዓት ግዥን በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር በሚደለደለው መሠረት ከባንክ በመርቸንዳይዝ ብድር የሚፈጸም ነው፡፡ ይህም በ2004 ዓ.ም ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ ብር 111,599,402 እና ለምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት ግዥ ብር 5,317,320,000 እንዲሁም በ2005 ዓ.ም ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ ብር 162,349,975 እና ለምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት ግዥ ብር 6,911,454,000 የተመደበላቸው ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ በ2004 ዓ.ም ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ ብር 98,110,147፣ ለምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት ግዥ ብር 9,937,740,000 እና በ2005 ዓ.ም ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ ብር 96,703,537፣ ለምርት ማሰደጊያዎች አቅርቦት ግዥ ብር 6,303,779,000 ሥራ ላይ አውለዋል፤ ይህ አፈጻጸም በፐርሰንታይል ሲታይ በ2004 እና 2005 ዓ.ም በቅደም ተከተላቸው የድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ 88% እና 59.6% እንዲሁም ለምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት ግዥ በቅደም ተከተላቸው 186.9% እና 91.2% ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል፡፡

## የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት

10. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የግብርና ምርት ማሣደጊያዎችን ከአገር ውስጥና ከውጪ አገር ገዝቶ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፣
2. የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች ዋጋ እንዳይንር የገበያ መረጋጋት መፍጠር፣
3. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ ናቸው፡፡

11. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት፡-

1. በአገሪቱ የግብርና ግብዓቶች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የድርጅቱን የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የግዥ፣ የሥርጭት እና የሽያጭ ዕቅድ ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ እንዲሁም በተያዘው ዕቅድና በጀት መሠረት ግዥ፣ ሽያጭና ስርጭቱን ተግባራዊ ማድረግ፣
2. የሚገዙትን የግብርና ግብዓቶች ዓይነታቸውን፣ መጠናቸውንና ይዘታቸውን እንዲሁም ዓመታዊ ዋጋቸውን በማቀነባበር እንዲፈቅዱ ማቅረብና ሲፈቀድም በድርጅቱ የግዥ መመሪያ መሠረት ግዥውን ማከናወን፣
3. የተገዙት የግብርና ግብአቶች በወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲጓጓዙ ማድረግና በትክክል ስለመድረሳቸው ማረጋገጥ፣
4. የድርጅቱ የምርት ግብአቶች ሽያጭ የሚጎለብትበትን ስትራቴጂ መቀየስና ሲፈቀድም በሥራ ላይ ማዋል፣
5. ድርጅቱ የሚገለገልባቸውን የሽያጭ አውታሮች መገምገም እና አስፈላጊ ጥናቶችን በማካሄድ የማሻሻያ ሐሳብ እንዲቀርብ ማድረግ፣
6. ለምርት ግብአቶች በቂና አስተማማኝ ማከማቻ መጋዘን እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
7. የድርጅቱ ግብርና ግብአቶች፣ ተሸከርካሪዎችና ሌሎችም ንብረቶች ተገቢው የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፣

12. በግብርና ሚ/ር የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

   1. ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የታወቁና የተመዘገቡ የግብርና ግብዓቶች ፍላጎት መተንበይ፣ ከአቅራቢዎች ጋር ማስተሳሰር፣ የአቅርቦትና የሥርጭት ክትትል ማድረግ፣
   2. በማዳበሪያ ፍላጎት ትንበያ ላይ በመመስረት ግዥውን መምራትና ማከናወን፣
   3. በምርጥ ዘር ፍላጎትና አቅርቦት ላይ በመመርኮዝ ክልላዊ የአቅርቦትና ሥርጭት ዕቅድ ማዘጋጀትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት በመለየት

የክፍተት ማሟያ ስልት መንደፍና ክልሎችንና ዘር አቅራቢዎችን በሥርጭት ዕቅድና ክፍተት ማሟያ ስልት ላይ በማወያየት ስምምነት መድረስና ማስተባበር፣

4. በግብርና ግብዓት ብዜት፣ አቅርቦት፣ ሥርጭት እና በጥራት ሂደት በሚገጥሙ ችግሮች ዙሪያ ጥናት ማካሄድ የተለያዩ ስልቶች በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆን መከታተል፣
5. በተለያየ እርከንና ደረጃ ለሚገኙ ባለሙያዎችና የግብይት ተዋንያኖች ስልጠና መስጠት/ማሰጠት/፣
6. የግብርና ግብዓት የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ለሚመለከታቸው የግብዓት ተዋንያኖች ሌሎች አካላት በሚፈለገው ወቅት ማሰራጨት፣ የመረጃ ሥርዓት ማዘጋጀትና መተግበር፣


13. የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. ለሕብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴ እና እድገት የሚበጁ የፖሊሲ ሃሳቦችንና የሕግ ረቂቆችን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
2. ባህላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት ወደ ዘመናዊ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚያድጉበት ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ የጥናቱንም ውጤት ያስተዋውቃል፣ ያሰራጫል፣ በተግባር መቶርጎሙንም ይከታተላል፣
3. በፌዴራል ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሳብ አጣሪ ይመድባል፣ ሲፈርሱም ከመዝገብ ይሰርዛል፣ በመላ ሀገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤
4. የሕብረት ሥራ ማኅበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ በሀገር ውስጥ ሸማቹና አምራቹ በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5. የሕብረት ሥራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት ወይም ዋጋ እንዲኖራቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እና የእጅ ጥበብ ምርቶች እንዲያድጉ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

6. የሕብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት የሚበጁ ፕሮጀክቶችን በማጥናትና በማዘጋጀት እንደአስፈላጊነቱ ከክልሎች ጋር በመተጋገዝ ማኅበራት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤
7. በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የሕብረት ሥራ ማኅበራት የምርት፣ የገበያ ኢንፎርሜሽንና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
8. በክልል ለሚደራጁ ቢሮዎችና የሕብረት ሥራ ማኅበራት የቴክኒክና የሙያ እገዛ ያደርጋል፤
9. ስለ ሥራው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤
10. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

## የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description)

14. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብዓቶች አቅርቦት ሥርዓት መነሻው ግብዓቱን የሚጠቀመው አካል ሲሆን ይህም በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ከየክልሉ የግብርና ጽ/ቤቶች የመጣውን መረጃ በማጠናቀር የግብዓት ግዥ ዕቅድና ፍላጎት ለግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሲያቀርብ የግዥ መመሪያ በሚያዘው መሠረት የጨረታ ስርዓቱን በማከናወን ግዥ እንዲፈጸም በማድረግ ግብዓቱን የማጓጓዝ፣ የመረከብ፣ የማከማቸት፣ ክፍያ የመፈጸም እና ሽያጭ የማካሄድን ሥራ ያከናውናል፡፡ ዝርዝር ሥዕላዊ መግለጫው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



## የኦዲቱ ዓላማ ፡-

15. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብርና ግብዓቶች ግዥ በትክክለኛ የተጠቃሚው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ፣ የስርጭት፣ ሽያጭ እና ክምችት ተግባሮችም ቀልጣፋ፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት የተላበሰና በዘርፉ የወጡትን ህግና ደንቦችን መሰረት ያደረገ እና ስርዓት የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት መካከል ተገቢው የሥራና የኃላፊነት ክፍፍል ማድረግና በመረጃው ልውውጥ ላይ በመመስረት የተቀናጀ ግዥ፣ የስርጭት፣ ሽያጭና ክምችት አስተዳደር ስርዓት የሰፈነ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሠራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (potential audit area) የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑ፤ ለግብዓት ግዥ ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ እንዲሁም የክምችት እና ስርጭት አፈጻጸምን መገምገም የሚመለከት ነው፡፡

## የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

17. በተመረጠው የኦዲት አከባቢ (potential audit area) ሥር ሦስት የኦዲት የትኮረት አቅጣጫ (audit issue) ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፡

1. የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የግዥ ሥርዓት የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ የተደራጀ የግዥ ሥርዓትን በመዘርጋት በወቅቱ ለተጠቃሚው ማድረሱን ማረጋገጥ፤

   1.1. በተጠቃሚው ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የግዥ ፍላጎት ስለመዘጋጀቱ፣

   1.2. በግዥ የቀረቡ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች በወቅቱ ለተጠቃሚው ስለመድረሳቸው ማጣራት፣

2. የምርት ግብዓት ማሳደጊያዎች ክምችትን ደህንነት ለማስጠበቅና የተቀላጠፈ አሠራር እንዲኖር ለማድረግ ለግብዓቶች በቂ፣ አስተማማኝ እና በሥርዓት የተደራጁ ማከማቻ መጋዘኖች መዘጋጀታቸውን ማጣራት፤

3. የምርት ማሳደጊያዎች ሥርጭት ሥርዓት የተጠቃሚው ፍላጐት እና አቅም መሠረት ያደረገና ግብዓቶቹም በወጣላቸው ኘሮግራም መሠረት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲጓጓዙ መደረጉንና በትክክል መድረሳቸውን እንዲሁም መሸጣቸውን ማጣራት፤

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፡-

18. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 52 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት፣የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1984 እና የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 174/1986 ዓ.ም፣የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት ማኑዋል ጥር 2004 ዓ.ም፣የማኔጅመንት አባላት የመስክ ሥራ ሪፖርት 2004 ዓ.ም፣የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የ5 ዓመት እስትራቴጂክ ዕቅድ፣የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ለኘራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የቀረበውን የ2004 እና 2005 በጀት ዓመት አመታዊ የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ የ2005 በጀት ዓመት የኦኘሬሽንና ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ ኘሮግራሞች ዕቅድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር **በአባሪ 1** ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ  ፡-

19. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፍነው ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችትና ስርጭት አፈጻጸምን በሚመለከት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሆኖ ከዚህ ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የግብርና ሚኒስቴር እና የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲን ያካተተ ሲሆን  በናሙና በተመረጡ አራት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ደርጅት ቅርንጫፍ ማዕከሎች (ነቀምት፣ በደሌ፣  ባህርዳር እና ወረታ) እንዲሁም በናሙና በተመረጡ አምስት ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና ሰባት መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ላይ ሲሆን ከግብዓት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ጋርም ውይይት ተካሂዷል፡፡ ኦዲቱም የተከናወነው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የየመ/ቤቶቹን  የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በቼክ ሊስት በመወያየት እና በማጣራት፣ ለግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አፈጻጸም ሥራ ላይ የዋሉ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በመገምገም ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲቱ ግኝቶች

**የምርት ማሳደጊያዎች በጥራት፣ በወቅቱና በዝቅተኛ ዋጋ ለአርሶ አደሩ መቅረቡን በተመለከተ፡-**

20. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጥራት ያላቸው የምርት ማሳደጊያዎች ወቅቱን ጠብቀው እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ ሊቀርቡ ይገባል፡፡

21. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከጥራት ጋር በተያያዘ ከውጭ ሃገር ሊገዙ የታቀዱ የጓሮ አተክልት ዘሮች ወይም ኬሚካሎች ጥራትን ለማስጠበቅ የግብዓቶቹ ናሙና ተልከው በግብርና ሚ/ር በኩል እንዲታዩ ሊደረጉ ሲገባ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የጥራት ፍተሻ የሚካሄድ መሆኑን፣ እንዲሁም ወቅትን ጠብቆ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ በቁጥር 5/004-5/05 በቀን 13/10/05 ዓ.ም ከማዕከላዊ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢያ ለግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት በተጻፈው መረጃ የአበባ ማዳበሪያ ተገዝቶ እንዲቀርብ ፍላጎት ቢቀርብም እስከ ታህሳስ 7/2006 ዓ.ም ያልቀረበ መሆኑን ፣ በማዕከላዊ ሽያጭና ሥርጭት ማዕከል በ2005 ዓ .ም ግንቦት እና ሰኔ አከባቢ መቅረብ የነበረበት ፀረ-አረም መደሃኒት መርጫ መሳሪያ በ2006 ዓ.ም ታህሳስ ወር እየቀረበ ያለበት ሁኔታ መኖሩን እና ግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከማዳበሪያ ውጪ ላሉ ግብዓቶች የሚደረገው የዋጋ ተመን ወጥ በሆነ መልኩ የትርፍ መጠን (profit margin standard) አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማደረጉን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ድርጅት ሽያጭ እና ሥርጭት ማዕከላት (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) እና በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን)፣ መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ/ደጋጊና፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) እንዲሁም በእነዚህ አከባቢ የሚገኙ 69 አርሶ አደሮችም ተጠይቀው

50 አርሶ አደሮች ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ጥራት የጎደለው (የኮረተ እና ማዳበሪያ ከረጢቱ የተቀደደ) ማዳበሪያ የሚቀርብላቸው መሆኑን፣ በወቅቱም የማይቀርብላቸው ይህም አንዳንዴ የአዝመራው ወቅት ሊያበቃ ሲል እና ካለፈም በኋላ የሚቀርብላቸው መሆኑን እና የፀረ-አረም መደሃኒትም ዋጋ ከ5- 10 ብር ድረስ ገበያ ላይ ካለው ብልጫ የሚያሳይ መሆኑን በኦዲቱ ለመለየት ተችሏል፡፡ (ዝርዝር የአርሶ አደሩ መልስ በአባሪ -2 ተያይዟል)



**ፎቶ ቁጥር አንድ ጥራት የሌለው ማዳበሪያ በሙቱሉ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር፤**



**ፎቶ ቁጥር 2 ጥራት የጎደላቸው የሥንዴ ዘር እና ማዳበሪያዎች በያያ ጀቦ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር**

23. በኦዲቱ ወቅት በታዩት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ለምን የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ለአርሶ አደሩ

ጥራቱን ጠብቆ በተመጣጣኝ ዋጋ የአዝመራው ወቅት ሳያልፍባቸው እንዲቀርብ እንደማይደረግ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ማዳበሪያና ሌሎች ግብዓቶች በቀጥታ ከውጭ ሀገር በህብረት ሥራ ማህበራቱ በኩል ቢመጡ የተጠቀሱት ችግሮች ላይኖሩ እንደሚችሉ እና ህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸውን የፋይናንስ ተቋም፣ በተጠናከረ ሁኔታ ባለማቋቋማቸው በመንግሥት ላይ ጥገኝነታቸው የቀጠለ መሆኑን ሲገልጹ፤ የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት በድርጅቱ በኩል ተገዝቶ የሚገባው ማዳበሪያ በቀጥታ ወደ አርሶ አደሩ የሚሰራጭ አለመሆኑን ፣ዩኒየኖች ከተረከቡ በኋላ በራሳቸው መጋዘን አከማችተው የሚያሰራጩ በመሆኑ ሊከሰት የሚችል መሆኑን ነገር ግን ዋጋን በተመለከተ ዋጋው ከጥራቱ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ፣ የአበባ ማዳበሪያን በሚመለከት የውጭ ምንዛሬ አላወራረዳችሁም በማለት የውጭ ምንዛሬው ሳይፈቀድ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ መቻሉን እና በሌሎች ግብዓቶች ላይ በርካታ አቅራቢዎች በመኖራቸው የትርፍ መጠኑን ይህን ያህል ነው ብሎ ማስቀመጡ እንደሚያስቸግራቸው ገልጸዋል፡፡

24. የግብርና ሚ/ር፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎቾ አቅራቢ ድርጅት በመቀናጀት ጥራት ያላቸው የምርት ማሳደጊያዎች ወቅቱን ጠብቀው እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ አለማቅረባቸው አርሶ አደሩ ማምረት የሚገባውን ምርት አምርቶ ውጤታማ እንዳይሆን  እና ወቅቱን ጠብቆ ግብዓቶች አለመቅረባቸው ግብዓቶቹ ለብልሽት እንዲዳረጉ ያደርጋል፤ እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ ምርት ማሳደጊያዎች አለመቅረባቸው አርሶ አደሩ ከላይ በተጠቀሱት እና  በኦዲቱ በታዩት መ/ቤቶች ላይ እምነት እንዳይኖረው ስለሚያደርግ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>**በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፡-**</u>

25.  የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት ሊያከናውኑ ይገባል፡፡

26. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ በበደሌ ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ በሚገኙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች፣  በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሁለት ዩኒየኞች (አምቦና በቾ)፣  አራት መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ እና ያያ ጀቦ) ፣ በአማራ ክልል በታዩ ሶስት ዩኒየኖች (መርከብ፣ፀሐይ እና ጎዛምን) እና 3 መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ)  ከማዳበሪያ ውጪ ያሉ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው በመሆኑ

ለአርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የእነዚህን ድርጅቶች ዋጋ እና ጥራት ከግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ዋጋ ጋር ለማነጻጸር እንዲሁም የትኞቹ ግብዓቶች ገበያ ላይ ተፈላጊነት አላቸው የሚለውን ለመለየት የሚያስችል፣ በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት እንደማያከናውኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. በኦዲቱ ወቅት በታዩት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት ያላከናወኑበትን ምክንያት ለሚመለከታቸው የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ምርት ማሳደጊያው በአሁኑ ጊዜ እየቀረበ ያለው በሌላ ድርጅት በመሆኑ የዋጋ ጥናት በህብረት ሥራ ማህበራት እንደማይደረግ፣ የህብረት ሥራ ማህበራት ምርት ማሳደጊያን ለመግዛት ምንም አማራጭ የሌላቸው በመሆኑ የቀረበላቸውን ብቻ ተቀብለው የሚያከፋፍሉ መሆኑን ሲገልጹ፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የገበያ ጥናት ልዩ ሙያ የሚፈልግ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በዋናው መ/ቤት የሰው ኃይል የሚሟላት ሥራ ተከናውኖ የጥናት ሥራው እንደሚጀምር ገልጸዋል፡፡

28. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት አለማከናወናቸው፤ አርሶ አደሩ የሚፈልጋቸውን የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን ዓይነት ለመለየት እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ የምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢዎቹ ዋጋቸውን ከሌሎች አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በማነጻጸር ለአርሶ አደሩ ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዳይቀርቡ ያደርጋል፡፡

***<u>ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-</u>***

29. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሚከናወነው ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን በፍላጎት ጥናት ላይ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

30. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና በታዩት በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች አርሶ አደሮች፣ ኢንቬስተሮች፣ የእርሻ

ልማቶች ወ.ዘ.ተ የሚፈልጉትን የምርት ማሳደጊያዎች መጠን ያሳወቁበት (ፍላጎት የተሰበሰበበት) መረጃ ተጠናቅሮ ሳይያዝ ያለፈውን አመት የግብዓት ፍላጎት መጠን በመነሳት ግዥ እንደሚፈጽሙ እንዲሁም በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች(አምቦ፣በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ/ደጋጊና፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) መህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ፍላጎት መጠን እና አይነት በልማት ሰራተኛው አማካኝነት ከእያንዳንዱ አርሶ አደር ተሰብስቦ በየደረጃው በሚገኙ እና ከአመራር አካላት በተዋቀረ ኮሚቴ ጸድቆ በግብርና ጽ/ቤቶች እየተጠናቀረ ለግብርና ሚ/ር ተልኮ በዚሁ መሰረት ግዥው ሊፈጸም ሲገባው በነኚህ በናሙና በታዩት ማህበራት ሥር የሚገኙ 69 አርሶ አደሮችም ተጠይቀው 35 አርሶ አደሮች የምርት ማሳደጊያዎችን ፍላጎት በየቀበሌው በሚገኙ ልማት ሰራተኞችም ሆነ በሌላ አካል ተጠይቀው እንደማያውቁ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

31. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የግብርና ሚ/ር እንደ አሰራር የግብርና ግብዓት ፍላጎት መሰብሰብ ያለበት በ1 ለ 5 አደረጃጀት እና በጣቢያ የልማት ሰራተኞች እያንዳንዱን አርሶ/ አርብቶ አደር በማማከር ነበር ከላይ በግኝቱ እንደተጠቀሰው የአሰራር ክፍተት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑ በሚመለከታቸው ክፍሎች የማስተካከያ ሥራ መሰራት እንዳለበት፣ በፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የምርት ማሳደጊያ ፍላጎት የሚሰበሰበው ወይም ተሞልቶ የሚቀርበው በግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሚገምቱት መሰረት እንጂ እያንዳንዱ የህብረት ሥራ ማህበራት አባል በሚፈልገው መጠን አለመሆኑን እና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናቱም ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር የተቀናጀ ባለመሆኑ የመረጃ አያያዝ ችግርም ሊፈጠር መቻሉን፣ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ወደፊት በተደራጀ እና በእያንዳንዱ ሽያጭ ጣቢያዎች እነዚህ መረጃዎች እንዲኖሩ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

32. የግብርና ሚኒስቴር፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሚከናወነውን ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን አለማድረጋቸው የምርት ማሳደጊያዎቹ በመጋዘን ጥበት ምክንያት ጥራት እንደይኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ በየዓመቱ የምርት ማሳደጊያዎች በብዛት በመጋዘን ውስጥ እንዲከርሙ እና ዋጋቸውም እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

**<u>የምርት ማሳደጊያዎች መጠናቸውን ጠብቀው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ስለሚደረገው ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ፡-</u>**

33. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ከክብደት በታች (Under Weight) የግብርና ግብዓት ከወደብ ወደ መሀል አገር እንዳይጓጓዝ በተለይም ተጠቃሚው ወደ ሆነው አርሶ አደር በቀጥታ እንዳይደርስ እንዲሁም ሾፌሩ ጭነት በጫነበትና ዕቃውን ወይም ጭነቱን ባስረከበበት ሰነዶች መካከል የባከነ ንብረት ወይም ልዩነት እንዳይኖር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባቸዋል፡፡

34. ከክብደት በታች (Under Weight) 50 ኪ.ግ. መሆን ሲገባቸው የማዳበሪያቸው ከረጢት ሳይፈታ ከ44- 49 ኪ.ግ. የሆኑ የምርት ማሳደጊያዎች በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወራታ)፣ ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) ፣ መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቡ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) እና አርሶ አደሮች ዘንድ እንደሚደርሱ በኦዲቱ ወቅት ለአርሶ አደሮቹ በተደረገው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፤(የአርሶ አደሮቹ ምላሽ ተጠናቅሮ **በአባሪ ሁለት** ተያይዟል፡፡) እንዲሁም በናሙና በተመረጡት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት በመጋዘን ውስጥ ለሚከሰቱ የግብዓቶች ፍሳሽ (ጉድለት) መጠን ድምር በየአመቱ ተጠናቅሮ በመረጃነት አለመያዙን ለመለየት ተችሏል፡፡

35. በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩት እና ከላይ በተጠቀሱት የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት ፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘኖች የሚገኙ ከክብደት በታች የሆኑ ማዳበሪያዎች ክትትል እየተደረገባቸው ወዲያውኑ ለሌላ ብክነት ሳይጋለጡ ሪባግ እንዲደረጉ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ16 ሐምሌ 2005 ዓ.ም ከግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት በተጻፈው ደብዳቤ ሾፌሮች 9,381.56 ብር የማዳበሪያ ጉድለት ያለባቸው ስለመሆኑ ለትራንስፖርት ዳይሬክቶሬቱ የተጻፈ ደብዳቤ እና በ01/07/05 ዓ.ም የኮንቦልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ሾፌሮች ያጎደሉትን 1,214.86 ከድርጅቱ ሂሳብ የቀነሰ መሆኑን ቢያመለክትም ድርጅቱ ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረጉን ከመረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

37. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ችግሩ ሊከሰት የቻለው ማዳበሪያውን በሚያስመጣው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና በአጓጓዥ ድርጅት መሆኑን፣ እንዲሁም ማዳበሪያው ወደብ ላይ ሲታሸግ ቀደም ባሉት አመታት የህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ማዳበሪያን ከውጭ ሲያስገቡ በነበረበት ወቅት እነዚህ ችግሮች ያልተከሰቱ መሆኑን ይህም የህብረት ሥራ ዩኒየኖቹና አደራጅ መ/ቤቶችም በወደብ በመገኘት ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጉ እንደ ነበር አሁን ግን በወደብ ላይ ሲታሸግ ቁጥጥር እና ክትትል አለመኖሩን ሲገልጹ፤ የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት ወደፊት የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጸዋል፡፡

38. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ከክብደት በታች (Under Weight) ማዳበሪያ ከወደብ ለተጠቃሚው አርሶ አደር እንዲደርስ ማድረጉ አርሶ አደሮቹ ከአቅራቢው ድርጅት እምነት እንዲያጡ ከማድረጉም በላይ አርሶ አደሮቹ ትክክለኛ መጠን የሌላቸውን ማዳበሪያዎች በመጠቀም ምርትና ምርታማነት እንዲቀንስ ያደርጋል እንዲሁም ሾፌሩ ጭነት በጫነበትና ዕቃውን ወይም ጭነቱን ባስረከበበት ሰነዶች መካከል የባከነ ንብረት ወይም ልዩነት እንዳይኖር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ እና የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

<u>የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ፣ ሥርጭት እና ክምችት መረጃ አያያዝን በተመለከተ፡-</u>

39. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ውሳኔ የተሰጠበትን ግብአት በተመላሽ የግብአት መረከቢያ ሰነድ (Stock Return Memo) ገቢ በማድረግ፣ ማዕከላዊ መጋዘኖችን የሚያስተዳድሩ የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት የክምችት መጠን አመልካቾችን (Inventory Control Indicators) ለተመረጡ ግብርና ግብአቶች በመጠቀም ክምችታቸውን እየገመገሙ የአቅርቦት ጥያቄያቸውን ለግብርና ግብአት ግብይት የሥራ ሂደት ሊያቀርቡ፤ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘኖች የማዳበሪያውን ዓይነት፣ የገባበትን ቀንና በድርድር ውስጥ የሚገኘው የማዳበሪያ መጠን፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ መለያ ካርድ(Bin Card) በድርድሩ ላይ በቀላሉ ለማየት በሚቻልበት ሁኔታ ሊንጠለጠል እና የገቢ፣የወጪ እና የሽያጭ መረጃዎችን ተጠናቅረው ሊይዙ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ፣ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ደርጅትበደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ ቅርንጫፎች በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ውሳኔ የተሰጠበት ግብአት በተመላሽ የግበአት መረከቢያ ሰነድ (Stock Return Memo) ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እንዲሁም በአማራ ክልል በሚገኙ ጸሃይ ዩኒየን ፣ መርከብ ዩኒየን እና ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ መሰረታዊ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ቢደረግም የማቀያየር ሥራ እንጂ ተመዝግቦ የሚያዝ አለመሆኑ፣ በድርጅቱ ሥር የሚገኙ ነቀምት እና ባህር ዳር ያሉ ማዕከላዊ መጋዘኖች በስራቸው የሚተዳደሩትን የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላትን የክምችት መጠን በየጊዜው የሚቆጣጠሩበትን ዘዴ ዘርግተው ተግባራዊ አለማድረጋቸውን በኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

41. በናሙና በታዩት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ቅርንጫፎች (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) በቅጽ 4 ገቢ የተደረገበት፣ በቅጽ 2(የታዘዘበት)፣ በቅጽ 5(ወጪ) ፣ በቅጽ 19 (ማርኬቲንግ ጣቢያዎች የሚረከቡበት ሰነድ) እንዲሁም ከቅጽ 3 (ለደንበኛ የሚሰጥ) ጋር ተነጻጽሮ የሚቀመጥበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት አለመኖሩን እና በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ባህር ዳር ዋናው ግቢ ባለው መጋዘን፣ በደሌ መጋዘን እና ነቀምት ሁለተኛው መጋዘን በቆርቆሮ የተሰራው (ከዋናው ግቢ ውጪ) ባለው መጋዘን ፣ በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) መጋዘኖች ውስጥ የማዳበሪያውን ዓይነት፣ የገባበትን ቀንና በድርድር ውስጥ የሚገኘው የማዳበሪያ መጠን፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ መለያ ካርድ(Bin Card) በድርድሩ ላይ አለመኖሩን እና በየጊዜው ክትትል እየተደረገ የማይሞሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

42. የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የህብረት ሥራ ኤጀንሲ የህብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ ቁጥጥር መላላት መሆኑን እንዲሁም በአብዛኛው የመጋዘን ኃላፊነት በመሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት የሚካሄደው በአርሶ አደሩ በመሆኑ የዕውቀት ችግር መኖሩን ሲገልጹ፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ወደፊት ታይቶ ስርዓቱ እና ሰነዶቹ እንዲዘጋጁ እንዲሁም የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖር እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

43. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ፣ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ግብዓቶችን የግዥ፣ ሥርጭት እና ክምችት  መረጃዎችን አጠናቅሮ አለመያዝ ለአሰራር እና ለቁጥጥር አመቺ እንዳይሆን እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች የሚቀመጡበትን ሥርዓት በተመለከተ፡-</u>

44. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች በመጋዘን  ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል፣ የመጋዘኑን ንጽህና ለመጠበቅ እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ ሊደረደሩ ፣ በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰቡ ግብዓቶች በተለየ ሥፍራ ፣ ሳይበላሹ እና ሳይጎዱ      የሚቀመጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም በሚወጡበት ወቅት አወጣጡ በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ  የገባው ቀድሞ ሊወጣ ይገባል፡፡

45. በናሙና ተመርጠው በታዩት በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል የሚገኙ ሰባት መሰረታዊ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ዲጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) በመጋዘኖች ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች በመጋዘኖቹ ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ አለመሆኑን፣ እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ መርከብ፣ ፀሐይ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ዲጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) በመጋዘኖች በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰቡ ግብዓቶች በተለየ ሥፍራ የማይቀመጡ መሆኑን እና ከላይ በተጠቀሱት ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ግብዓቶቹ በሚወጡበት ወቅት አወጣጣቸው በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ  የገባው ቀድሞ እንዲወጣ አልተደረገም፡፡

46. ስለ ጉዳዩ የግብርና ሚ/ር፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የምርት ማሳደጊያዎች በህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘኖች ውስጥ የሚከማቹት ከህብረት ሥራ ማህበራቱ ፍላጎት ውጪ በመሆኑ የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱና ማህበራቱ ለተለያዩ ወጪዎችም እንደሚዳረጉ ፣ የምርት ማሳደጊያዎችም በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ተገዝተው ሲበላሹና ለብክነት ሲጋለጡ የሚታይ መሆኑን ይህም በተለይ የምርጥ ዘር ፍላጎት ሳይጠናና የኤክስቴንሽን ሥራው ሳይካሄድ በኮታ ብቻ እንዲመጣ በመደረጉ ለክምችት በመዳረግ ሊበላሹ መቻላቸውን እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች

አቅራቢ ድርጅት ይህን በሚመለከት ለወደፊት በጀት ተይዞላቸው የሚስተካከልበት ሁኔታ ይኖራል ብለው ገልጸዋል፡፡

47. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች የሚቀመጡበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የምርት ማሳደጊያዎቹ ለብልሽት እንዲዳረጉ በር ይከፍታል፣ የግብዓቶቹ ጥራት እንዲጓደል በማድረግ አርሶ አደሩ እጅ ሲገቡ በምርት ላይ ተጽኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

<u>**የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘን አያያዝ፣ ጥራት እና የመገልገያ መሳሪያዎችን በተመለከተ፡-**</u>

48. የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘኖች ሕንጻ አሰራር ጥራታቸውን የጠበቁ ሆነው በየጊዜውም ክትትል ተደርጎ ተገቢው ጥገና ሊደረግላቸው እና በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የመገልገያ መሳሪያዎችም በመጋዘኖቹ ውስጥ ተሟልተው ሊገኙ እንዲሁም የምርት ማሳደጊያዎች አያያዝ ሁኔታ በሚመለከተው ኃላፊ በየጊዜው ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

49. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሥር በሚገኙ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከአራቱ(ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች በሶስቱ(ነቀምት፣ በደሌ እና ባህር ዳር) ጣቢያዎች ፣ ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ሙቱሉ፣ ዱጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ከግብርና ግብአቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንብረቶች(የማዳበሪያ ከረጢቶች፣ ጆሪካን፣ ካርቶኖች፣ በርሚሎች፣ ማገዶዎች፣ ቆርቆሮዎች፣ ሌሎች ግብዓቶች ተቀላቅለው (ብረት ነክ/ቢቢኤም የእርሻ መሳሪያ እና ማዳበሪያዎች…) በክምችት መጋዘን ውስጥ ተጣበው እንደተቀመጡ እና ንብረቶቹም ተሸጠው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም መወገድ ያለባቸው እንዲወገዱ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት በተካሄደው የመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡



ፎቶ ቁጥር 3 BBM የእርሻ መሳሪያ እና ማዳበሪያ ተቀላቅሎ የተቀመጠበት ሙቱሉ መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር፤



ፎቶ ቁጥር አራት በበቾ ዩኒየን መጋዘን ውስጥ ባዶ የማዳበሪያ ከረጢቶች እና ካርቶኖች ከምርት ማሳደጊያዎች መጋዘኖች ውስጥ፤



ፎቶ ቁጥር አምስት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የነቀምት መጋዘን የተለያዩ ካርቶኖች እና የማዳበሪያ ከረጢቶች ጋር ግብዓቶች ተቀላቅለው የተቀመጡበት ሁኔታ፣

50. ለየመጋዘኖቹ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት(ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ)፣ ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራትማህበራት(ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) በሚገኙ መጋዘኖች ውስጥ አገልግሎት ላይ መዋል የሚገባቸው የመገልገያ መሳሪያዎች (አካፋና ዶማ ፣ ሴንጢ፣ መሰላል፣ የናሙና መያዣ ከረጢት፣ የኬሚካል ቱታ፣ የፊት እና የዓይን መሸፈኛ (ጎግልና ማስክ)...) አለመሟላታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሱት አከባቢዎች በሚገኙ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የመጋዘን ሕንጻ አሰራር ጥራቱ የጠበቀ ሆኖ በየጊዜውም ክትትል ተደርጎ ተገቢው ጥገና እንደማይደረግላቸው በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡- የፀሐይ ዩኒየን፣ ደጋጊና እና ምስራቅ ጮራ መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር መጋዘኖች ዝናብ የሚያስገቡ መሆኑን ሲሆን ከላይ በተጠቀሱት መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የመጋዘኖች ከግብዓቶች ማከማቻነት በተጨማሪ ለጤና ችግር እና ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ ሠራተኞች እንደ ቢሮ እንደሚጠቀሙባቸው በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡



ፎቶ ቁጥር ስድስት የደጋጊና መሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበር መጋዘን ወለል እና ግርግዳ አሰራር፤

51. ስለ ጉዳዩ የግብርና ሚ/ር፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የግብርና ሚ/ር አሁን ክፍተቱ የታየው በክልል/ በዞን ያሉ ሥልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች በነበሩበት ቦታ ባለመቆየታቸውና በየዓመቱ የወሰዱትን ሥልጠና ለማሕበራት ባለመስጠታቸው መሆኑን፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ይህንን መጋዘን ለመገንባት የሚያስችል አቅም የሌላቸው ህብረት ሥራ ማህበራት መኖራቸውና እነኝህን መጋዘኖችም ለመገንባት የሚያስችል ግንዛቤ አለመኖሩን እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት አስፈላጊነቱ የሚታመንበት እና ለወደፊት በጀት ተይዟላቸው አስፈላጊው ሁሉ እንዲሟላላቸው የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

52. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የግብዓት ማከማቻ መጋዘኖች ጥራታቸውን ያልጠበቁ መሆናቸው እና በውስጣቸውም የሚያስፈልጉ መገልገያ መሣሪያዎች አለመሟላታቸው የምርት ማሳደጊያዎች ለብክንት ወይም ለብልሽት እንዲዳረጉ ያደርጋል፣ እንዲሁም የመገልገያ መሳሪዎች አለመሟላታቸው በሰው ጤና ላይ ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

**የሚወገዱ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸውን የግብርና ግብዓቶች አያያዝ በተመለከተ፡-**

53. በማንኛውም ምክንያት በማዕከል እና በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት መጋዘኖች ሊወገዱ የሚገባቸው፣ ለተጠቃሚ ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብአቶች ዝርዝር ሊያዝና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

54. በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በሚገኙ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ መርከብ፣ ፀሃይ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) መጋዘኖች የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚው ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብዓቶች ዝርዝር ተጠናቅሮ የማይያዝ እና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው አለመደረጋቸውን በኦዲት ወቅት በተካሄደ የመስክ ጉብኝት ለማየት ተችሏል፡፡

55. ይህም በናሙና ተመርጠው በታዩት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭ እና ሥርጭት ማዕከላት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ግብዓቶች (የጓሮ አተክልቶች 2.3 ኪ.ግ ፣ አግሮ ኬሚካል 2,375 ሊትር፣ አክቴሊክ 2% 1,573 ሊትር እና ሴቪን 46 ጠቅላላ የብር ግምታቸው 671,941 እንዲሁም 56 አይነት የእንስሳት መደሃኒቶች እና መገልገያ መሳሪያዎች) አይነት መኖራቸው በመስክ ኦዲት ከተከለሱ ዶክመንቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በቁጥር 4/05 ቀን 06/05 2005 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በክልሉ ውስጥ አገልግሎት ላይ የማይውሉ ማዳበሪያ በመሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒየኖች ዳፕ 15,065.05 ኩንታል፣ ዩሪያ 12,935.68፣ ላይም ውህድ 433 ኩንታል፣ ኦርጋ 58.5 ጥቅም ላይ የማይውል ምርጥ ዘሮች(በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ ቦሎቄ፣ አኩሪ አተር፣ ሽምብራ ፣ ማሽላ እና ለውዝ) 32,472.29 ኩንታል መኖሩን እና የኦዲት ቡድኑ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን ተገኝቶ ባካሄደው የመረጃ ክለሳ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ግብዓቶች በሲ-1/122 ቀን 09/07/05 በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት በ18 ወረዳዎች ዳፕ 2,590 ኩንታል፣ ዩሪያ 2,246 ኩንታል፣ የአረም መደሃኒት 4,487 ሊትር እና የተለያዩ ዘሮች(ስንዴ፣ በቆሎ፣ ባቄላ ገብስ ፣ ጤፍ እና ሽንብራ) 3,333.7 ኩንታል መኖራቸው ቢታወቅም ፣እነዚህ ግብዓቶች ለብክነት ሳይጋለጡ እንዲሸጡ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲወገዱ አለመደረጋቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡



ፎቶ ቁጥር ሰባት በአዋሽ ቡኔ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያለው የBBM እርሻ መሳሪያዎች እና የተበላሹ ማዳበሪያዎች፤

56. ስለ ጉዳዩ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ይህ መረጃ በእነርሱ በኩል የማይታወቅ መሆኑን እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት አብዛኛው ከዚህ በፊት የተወገዱ ሲሆን ኬሚካልን በተመለከተ በሀገር ደረጃ በግብርና ሚ/ር አማካኝነት ቀሪዎቹ እንዲወገዱ እንዲሁም ሌሎቹንም በመለየት የማስወገዱ ሥራ እንዲከናወን ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

57. በግምርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ፣ በዩኒየኖቹ እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ሊወገዱ የሚገባቸው እና አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው ግብአቶች ተመዝግበው ውሳኔ ካላገኙ የመጋዘን ጥበት ከመፍጠራቸውም በላይ መወገድ የሚገባቸው ሌላ በክምችት መጋዘን ውስጥ ያሉ ግብዓቶችን ሊበክሉ እና ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

**ድርጅቱ ፣ የግብርና ሚ/ር እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የሽያጭ ማዕከላት የሚያካሂዱዋቸውን የሽያጭ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ፡-**

58. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የሽያጭ ጣቢያዎች የሚያካሂዱዋቸውን የግብዓቶች ሽያጭ ከብክነት እና ከምዝበራ ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ የድርጅቱ የሽያጭ ጣቢያዎች በሽያጭ ሰራተኞች አላስፈላጊ ብክነት እና ምዝበራ እንዳይፈጸም ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋና ሥራ ላይ እንዳልዋለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ፡- በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭ ጣቢያዎች የሚሰሩትን ሥራ እንዲሁም የሚሸጡበትን ሥፍራ በመቆጣጠር ለይቶ አለማወቃቸውን፣ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ያለ ዋስትና ለአርሶ አደሮች የግብዓት ማከማቻ መጋዘን እና ገንዘብ የመሰብሰቡን ሂደት እንዲያስተዳድሩ እየተደረገ አንድ አርሶ አደር እስከ ብር 135,080.26 የመዘበረ በመሆኑ በምዕራብ ሸዋ ዞን ፍርድ ቤት የተፈረደበት ቢሆንም ያለው ንብረት መጠን ብር 32,380 ብቻ በመሆኑ ብር102,700.26 ለወደፊት ንብረት ሲያፈራ እንዲከፍል መባሉን ለሜታ ሮቢ ወረዳ በቁጥር ABWHG/M-12/121 ቀን 22/12/2004 ዓ.ም ከተላከው ደብዳቤ እና መረጃ መታወቁን እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በ6 መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙ 7 አርሶ አደሮች ብር 485,293 ያባከኑ ሲሆን ጉዳያቸውም በፍርድ ቤት ሂደት ላይ መሆኑን ከደቡብ ም/ሸዋ ዞን የሕብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ከተገኘው መረጃ መታወቁን እና እንዲሁም በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ወንበርማ ወረዳ ወገደድ መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬውች ህብረት ሥራ ማህበር ያለ ዋስትና ለአርሶ አደሩ የግብዓት ማከማቻ መጋዘን እና ገንዘብ የመሰብሰቡን ሂደት እንዲያስተዳድር እየተደረገ አንድ አርሶ አደር እስከ 1,626,033.62 ብር የመዘበረ መሆኑ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የተፈረደበት ቢሆንም ያለው ንብረት ከዚህ ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ በእስር እንዲቀጣ እና ወደፊት ንብረት ሲያፈራ እንዲከፍል በሚል ውሳኔ የተሰጥበት ሁኔታ መኖሩን በ መ/ቁ 0158174 ቀን 30/11/2005 ዓ.ም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በጻፈው መረጃ መታወቁን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

60. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እዛ በማዕከል የሚገኙ ኃላፊዎች የቁጥጥሩን ሥራ ይሰራሉ በማለት ብዙም ክትትል አለማድረጋቸውን እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ በራሳቸው የሚተዳድሩ በመሆኑ የቁጥጥር ሥርዓቱን ሊያጠናክር የሚያስችል የአቅም ውስንነት ያለባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

61. ድርጅቱ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማት በተለያዩ አከባቢዎች የሚገኙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን ከብክነት እና ከምዝበራ ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያለመዘርጋታቸው የአሰራር ክፍተት በመፍጠር ለአላስፈላጊ ብልሹ አሰራር በማጋለጥ ተቋማቱ የተቋቋሙበትን ዓላማ እንዳያሳኩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**<u>የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭትና ክምችት አፈጻጸም ሪፖርትን በተመለከተ፡-</u>**

62. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና በሌሎች አስፈጻሚዎች የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የግብዓት ግዥ፣ ክምችት፣ ሥርጭት እና ሽያጭ እንቅስቃሴ በወር፣ በሩብ ፣ በግማሽ አመትና በአመት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ግብዓቱ አይነት በቀን ወይም በሳምንት ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡

63. ይሁን እንጂ በድርጅቱ እና በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ሥር በሚገኙ ማከፋፈያ መጋዘኖች ሥለተደረገው ሽያጭ በማጠቃለል የሽያጭና የሥርጭት ማዕከሉ በየሳምንቱ ለዋናው መ/ቤት ለሽያጭና ሥርጭት ቡድን ሪፖርት እንደሚያደርጉ ለኦዲት ቡድኑ የሥራ ኃላፊዎች የገለጹ ቢሆንም ይህን ሁኔታ የሚያረጋግጥ የተጠናቀረ ሪፖርት አልተገኘም፡፡ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩ እና ከላይ በቁጥር 54 ላይ በተገለጹት ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሳይሆን ሽያጭ በብዛት በሚከናወንበት ወቅት ብቻ የተሸጠውን መጠን ብቻ የሚያሰውቁ መሆኑን እንጂ ቀጣይነት ባለው መልኩ በወር፣ በሩብ፣ በግማሽ አመት እና በአመት ሪፖርት የማያዘጋጁ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. የህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት ተጠይቀው፣ የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ህብረት ሥራ ማህበራት በተጠየቁበት ወቅት የሽያጭ መጠኑን ብቻ እያሳወቁ የሚሄዱበት ሁኔታ እንጂ እስካሁን ባለው ወጥ በሆነ መልኩ ሪፖርት አለማቅረባቸውን እና የግብርና ምርት ማሳደጊያች አቅራቢ ድርጅት ወደፊት ሁሉም ሽያጭ ጣቢያዎች እቅድ እንዲያዘጋጁ እና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

65. በወር፣ በሩብ ፣ በግማሽ አመትና በአመት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ግብዓቱ አይነት በቀን ወይም በሳምንት ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሪፖርት አለመዘጋጀቱ የቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓቱ የላላ መሆኑንና የተጠናከረ ተጠያቂነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

<u>የምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-</u>

66. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በተዘጋጀውም የሥርጭት ፕሮግራም መሠረትና ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ በመመርኮዝ የግብርና ግብዓት ሥርጭት ሊፈጸም፣ የሚያጓጉዝበትን የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የጣቢያዎችን ዝርዝር የያዘ የስርጭት ፕሮግራም ተጠናቅሮ ሊያዝ እና ሥምሪት የወሰደው ሾፌርም በተሰጠው ስምሪት መሰረት ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጀል ተብሎ በተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መሰረት መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

67. በናሙና በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ፣በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት( ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋ ሽቡኔ እና ያያ ጀቦ) ፣በአማራ ክልል በሚገኙ መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት( ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ)፣ በኦሮሚያ እና አማራ ክልል የሚገኙ ዩኒየኖች (በቾ፣ አምቦ፣ ጸሃይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የያዘ የሥርጭት ፕሮግራም እንደማያዘጋጁ እና መረጃዎቹንም አጠናቅረው የማይዙ መሆኑን፣ እንዲሁም በምስራቅ ጮራ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር አንድ መኪና ዳፕ ማዳበሪያ ተጠይቆ አንድ መኪና ዩሪያ ማዳበሪያ እንዲረከቡ መደረጉን ፣ ከላይ በተጠቀሱት እና በናሙና በታዩት የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የምርት ማሳደጊያዎች ከጠየቁት ቁጥር በላይ ወይም በታች የሚላክላቸው መሆኑን ለኦዲቱ ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

68. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በሀገር ውስጥ ለሚደረገው የከባድ መኪና ተሽከርካሪዎች ጉዞ ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጀል ተብሎ የተወሰነው የጉዞ

ሰሌዳ መመዘኛ (standard) ተዘጋጅቶ ተሸከርካሪው መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩን ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. ስለሁኔታው የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ህብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚያሰራጩበት የራሳቸው የሆነ መንገድ እንደሚኖራቸው እና ከቦታ ቦታም እንደሚለያይ ይህም ለወደፊት የሰው ሃይል ቀጥረው የሚያሰሩበት ሁኔታ ሲፈጠር የሥርጭት ፕሮግራም ሳያስፈልግ ሁልጊዜ ሽያጭ እንዲያከናውኑ እንደሚደረግ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭ ጣቢያዎች ይህን ያህል እንፈልጋልን ብለው ሲያቀርቡ የሚላክላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

70. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በተዘጋጀውም የሥርጭት ፕሮግራም መሠረትና ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ በመመርኮዝ የግብርና ግብዓቶች ሥርጭት አለመፈጸማቸው አርሶ አደሮቹ ከሚፈልጉዋቸው በላይ/በታች የሆኑ ግብዓቶች በገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ወይም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች በክምችት እንዲቆዩ/ አርሶ አደሮች የሚፈልጉዋቸውን ግብዓቶች በተሟላ መልኩ እንዳያገኙ ስለሚያደርግ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>**የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች በስርጭት አውታሮች፣ በአከባቢ እና በገበያ ሁኔታ የሚለዩ መሆናቸውን በተመለከተ፡-**</u>

71. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ መለየት ይኖርበታል፡፡

72. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች(በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) እንዲሁም በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በታዩት ባህር ዳር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጎንደር፣ አምቦ፣ ወሊሶ፣ በደሌ እና ነቀምት የሚገኙ የግብርና እና የህብረት ሥራ ማህበራት ጽ/ቤቶች ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ የሚለዩበት ሁኔታ ይኖራል ቢሉም የምርት ማሳደጊያዎቹ ዓይነት ዝርዝር እና የሚፈለጉበት ቦታ በመረጃነት ተጠናቅሮ አለመያዙን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

73. የህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የምርት ማሳደጊያዎችን በሙሉ ኃላፊነቱን የወሰደው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት መረጃው መያዝ እንዳለበት እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የድርጅቱ ሽያጭ ዕቅድ የሽያጭ ጣቢያዎችን መሰረት ያደረገ ሲሆን የመረጃ አያያዝን በተመለከተ በየጣቢያዎቹ የሚፈለጉ ግብዓቶች ዝርዝር እና የሚፈለጉበት ቦታ መረጃዎች ተደራጅተው በተጠናከረ መልኩ እንዲያዝ ለወደፊት ይደረጋል ብለው ገልጸዋል፡፡

74. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ አለመለየቱ ግብዓቶቹ ወደ ማይፈለግበት ቦታ እንዲሄዱ በማድረግ አቅራቢዎቹ ለሌላ ሽግሽግ ወጪ እንዲዳረጉ ከማድረጉም በላይ በሽግሽግ ወቅት ግብዓቶች ለምዝበራ ወይም ለብክነት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

<u>**የምርት ማሳደጊያዎችን ማስተዋወቅ እና የሽያጭ አውታሮችን ማስፋፋትን በተመለከተ፡-**</u>

75. የምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት የሚገኙ ግብዓቶች ወደ ደንበኛው ቀርበው ሊተዋወቁ፣ በምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭት እና ክምችት ዙሪያ ለተሰማሩ ሠራተኞች ሙያቸውን ለማሻሻል እንዲችሉ ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው፣ ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ያሉበትን ሥፍራ ሊጠቁሙ የሚችሉ ማስታወቂያዎች ሊኖሩ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ኢኮኖሚያዊ የማከፋፈያና የሽያጭ አውታሮችን ሊዘርጋና በየጊዜው እንዲሻሻሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

76. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ መርከብ፣ ፀሃይ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) የግብዓቶች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት በሚገኙ የምርት ማሳደጊያዎች ላይ የማስተዋወቅ ሥራ የማይሰራ መሆኑን፣በግብዓት ማከማቻ መጋዘን ለሚሰሩ ሰራተኞች የምርት ማሳደጊያዎች አያያዝ እና አጠቃቀም ሁኔታን በተመለከተ ሥልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና ከታዩት አራቱ( በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች በሁለቱ (በባህር ዳር እና በበደሌ)

፤በናሙና ተመርጠው ከታዩት አምስት ዩኒየኖች በአንዱ (ጸሃይ) እና የህብረት ሥራ ማህበራት ( ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ሙሉ በሙሉ የጣቢያዎቹን ሥም የያዘ ማስታወቂያዎች ወይም ምልክቶች የሌሉ ሲሆን በቀሪዎቹ ጣቢያዎች ደግሞ የቆዩ እና በደንብ የማይታዩ እና የማይነበቡ መሆናቸውን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

77. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በየጊዜው ልዩ ልዩ የሽያጭ ሥልቶችን በመንደፍ የሽያጭ መጠኑ እንዲጨምር እና የድርጅቱ ትርፋማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ የሽያጭ አውታሮችን ያልዘረጋና በየጊዜው እንዲሻሻሉ አለማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በበጀት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መሰረት ድርጅቱ በ2004 ዓ.ም ያስገኘው ትርፍ 35,378,193 ሲሆን በ2005 ዓ.ም ግን 16,126,271.34 መሆኑ ታውቋል፡፡

78. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የግብርና ሚ/ር፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የግብርና ሚ/ር ማህበራት ሁሉንም ግብዓት በተሟላ መልኩ ለአባሎቻቸው የሚያቀርቡበት የዕቅድ ማነስ ጋር ተያይዞ ነው እንጂ እንደ አላማቸው ከታየ ድርሻቸው መሆኑንና ለወደፊት ማህበራት ሁሉንም ግብዓት ለአባሎቻቸው ማቅረብ እንዲችሉ የማጠናከር ሥራ በተጠናከረ መንገድ መሰራት እንዳለበት እንዲሁም ሥልጠናው በየጊዜው የሰለጠነው አካል ከቦታ ወደ ቦታ ስለሚዘዋወር የተፈጠረ ችግር መሆኑን፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ከግንዛቤ ማጣትና ትኩረት ካለመስጠት የተነሳ እና የግዥ ቦታውን አባላት ያውቁታል በማለት ከመዘናጋት የመጣ ችግር መሆኑን እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ድርጅቱ ቀድሞ በነበረው በራሱ ማዳበሪያዎችን ይሸጥ ስለነበር እና አሁን ለዩኒየኖች የማስረከብ ሥራ እያከናወነ በመሆኑ ክፍተት ያሉባቸው ቦታዎች ላይ ብቻ ሽያጭ እንዲከናወን በመደረጉ ጣቢያዎች የቀነሱ መሆናቸውን፣ ሌሎች ግብዓቶችን በተመለከተ ወደፊት እየታየ እንዲስፋፉ እንደሚደረግ እና ሥልጠናን በተመለከተ አሁን ኦረንቴሽን ይሰጣል ነገር ግን ለወደፊት ብሮሸሮች እንዲሁም ሥልጠና እንዲዘጋጅ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

79. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች እንዲተዋወቁ እና የሽያጭ አውታሮች እንዲስፋፉ አለመደረጉ እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዙሪያ የተሰማሩ ባለሙያዎች ስልጠና አለመውሰዳቸው አቅራቢዎቹ የሚያቀርቡትን ግብዓቶች ተጠቃሚዎቹ አውቀው እንዳይገዙ በማድረግ አቅራቢዎቹ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም በግብዓቶች አያያዝ ዙሪያ ለመጋዘን ሰራተኞቹ ስልጠና አለመሰጠቱ ግብዓቶቹ ጥራት ባለው መልኩ እንደይቀመጡ በማድረግ የግብዓቶቹ ጥራት እንዲጓደል ያደርጋል፡፡

## የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዱቤ ሽያጭን በተመለከተ፡-

80. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ የተፈቀደውን የክሬዲት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በአመት ውስጥ በዱቤ ሊሸጥ የታቀደው የግብዓት ዋጋን ሊተመኑና ለመሰብሰብም ፕሮግራም ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡

81. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከ2004- 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በድርጅቱ የክሬዲት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማድረጉን እና በአማራ ክልል በ15 ዩኒየኖች አማካኝነት ለአርሶ አደሮች በዱቤ የተሰራጨ እና ያልተሰበሰበ የምርት ማሳደጊያዎች ብር 706,792,927.56 መሆኑን ከABKM agricultural input loan for the year 2004/2005 E.C የተገኘ መረጃ ቢያመለክትም ይህን ብድር የግብርና ጽ/ቤቶች፣ የህብረት ሥራ ጽ/ቤቶች፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት በቅንጅት ወቅቱን ጠብቀው የማያስመልሱ መሆኑን በክልሉ የሚገኙ እና በናሙና በታዩ መርከብ፣ ጸሃይ እና ጎዛምን ዩኒየን ባለሙያዎች በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

82. እንዲሁም በአማራ ክልል ለኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 37 አርሶ አደሮች ተጠይቀው 37ቱም ብድር የአዝመራው ወቅት መጨረሻ ላይ ስለሚሰጣቸው ይህ በአርሶ አደሩ ዘንድ የታወቀ በመሆኑ ብድሩን በመጠበቅ በጥሬ ገንዘብ መግዛት እየቻሉ ብድር ጠብቀው ግብዓቶቹን እንደሚያገኙ ታውቋል ፡፡

83. የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ግብዓቶችን በመስጠቱ ወይም በማሰራጨቱ ሂደት የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚሳተፉ ቢሆንም ብድር በማስመለሱ ሂደት ይህ አይነት ቅንጅታዊ ሥራ እንደሌለ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በቅርብ ጊዜያት የዱቤ ሽያጭ ፍላጎት እየቀረበ በመሆኑ የዱቤ ሽያጭ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርድ የቀረበ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

84. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የክሬዲት ፖሊሲ አውጥቶ ተግባራዊ አለማድረጉ በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በማድረግ ድርጅቱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም በአማራ ክልል ለአርሶ አደሩ በዱቤ የተሰራጩ የምርት ማሳደጊያዎች በወቅቱ አለመሰብሰባቸው የህብረት ስራ ማህበራቱ እንዲዳከሙ ስለሚያደርግ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ለሚሸጡ የምርት ማሳደጊያዎች የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ብዛት መመዘኛ ደረጃ መዘጋጀቱን በተመለከተ፡-**

85. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ... ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) ሊያዘጋጁና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የቅጣት አሠራር ሊዘረጉና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች(በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) እንዲሁም በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በታዩት ባህር ዳር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጎንደር፣ አምቦ፣ ወሊሶ፣ በደሌ እና ነቀምት የሚገኙ ዩኒየኖች እና የህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ... ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) አለመዘጋጀቱን እና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የቅጣት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን እንዲሁም በነዚህ መጋዘኖች የሚገኙ ሰራተኞችም የተረከቡትን ሙሉ በሙሉ እንደሚጠየቁ በኦዲቱ ወቅት ለመለየት ተችሏል፡፡

87. ስለሁኔታውየፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ይህን ለማከናወን የግንዛቤ እና የአቅም ችግር መኖሩን እና በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በቀጣይ ጥናት በማድረግ የፈሳሽ፣ የሥባሪ ወይም የብልሽት ደረጃ የሚወጣ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

88. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ... ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዙሪያ የሚሰሩ ሰራተኞችን ብቃት ለመለየት ካለማስቻሉም በመጋዘን የተሰማሩ ሰራተኞች ለፈሰሰው ወይም ለተበላሸው መጠን ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ እንዲሆኑ ሥለሚያደርግ የሰራተኞቹን የሥራ ተነሳሽነትን ይቀንሳል፡፡

**ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች ትኩረት መስጠትን በተመለከተ፡-**

89. ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ የግብርና ግብዓቶች ትኩረት ሊሰጥ እንዲሁም ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡

90. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና በታዩት አራቱ( በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች ያሉት ግብዓቶች ውስን መሆናቸውን እና የላብራቶሪ እቃዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች የተለያዩ የጓሮ አተክልቶች፣ የእንስሳት መደሃኒቶች፣ የአበባ ማዳበሪያዎች … በጣቢያዎቹ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት በተካሄደው የመስክ ጉብኝት ለማረጋገጥ ተችሏል፤ እንዲሁም በነዚህ አከባቢ የሚገኙ ዩኒየኖች ፣ ማህበራት፣ የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች እና የግብርና ጽ/ቤቶችም ሌሎች ግብዓቶች በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እንደሚቀርቡ የማያውቁ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ከላይ በተጠቀሱት አከባቢ የሚገኙ 69 አርሶ አደሮች ተጠይቀው የተለያዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ፍላጎት ቢኖራቸውም ሙሉ በሙሉ ከ2004 ዓ.ም- 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የሚቀርቡላቸው ግብዓቶች ማዳበሪያዎች፣ ፀረ-አረም እና የተለያዩ የህል ምርጥ ዘሮች ብቻ መሆናቸውን እና በግብርና ምርት ማሳደገያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

91. ስለጉዳዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከማዳበሪያ ውጪ ያለው አቅርቦት የተቀራረጠ በመሆኑ ቀደም ሲል ሲታወቅ በነበረው ሁኔታ ባለመሆኑ የግንኙነት ክፍተት መኖሩ የታወቀ ስለሆነ ክፍተቱን ለማየት እና የተጠናከረ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

92. ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች ትኩረት አለመሰጠቱ የአርሶ አደሮች ምርትና ምርታማነትን ከመጨመር አኳያ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሊያበረክት ይችል የነበረውን አስተዋጽኦ እንዲቀንስ አድርጓል፤ እንዲሁም ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ አለመቀመጡ ከማዳበሪያ ውጪ ያሉ ግብዓቶችን በአግባቡ በማስተዋወቅ ሊፈጠር ይችል የነበረውን ግንዛቤ እንዳይፈጠር አድርጓል፡፡

**የምርት ማሳደጊያዎች እጅ በእጅ ሽያጭ ባንክ ገቢ መደረጉን በተመለከተ፡-**

93. በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ በተከሄደበት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ባንክ ካለ በዕለቱ እና ባንክ ከሌለ ሠራተኛው የሰበሰበውን ጥሬ ገንዘብ በካዝና በማስቀመጥ በሶስት ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ባንክ በመሄድ ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

94. ሆኖም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት(በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ሲከናወን በዕለቱ ባንክ ገቢ እናደርጋለን ቢሉም በየቀኑ የተሰበሰበው መረጃ ባንክ ከገባበት(slip) ጋር ተነጻጽሮ መቅረብ አለመቻሉን እና በቾ፣ አምቦ፣ መርከብ፣ ጸሃይ እና ጎዛምን ዩኒየኖች እንዲሁም ሙቱሉ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ሲከናወን የተሰበሰበውን ገንዘብ እስከ አንድ ወር ድረስ በአርሶ አደሩ እጅ የሚቆይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ኃላፊዎች እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በማህበራቱም ደንብ መሰረት ከባንክ በራቁ ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ወዲያውኑ ባንክ ገቢ መደረግ እንዳለበት ከዚህ ውጪ ግን ከሆነ መጠየቅ እንዳለባቸው እንደሚያስቀምጥ እና በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የመረጃ አያያዝ ችግሮችን በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

96. በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ በተከሄደበት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ባንክ ካለ በዕለቱ እና ባንክ ከሌለ ሠራተኛው የሰበሰበውን ጥሬ ገንዘብ በካዝና በማስቀመጥ በሶስት ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ባንክ በመሄድ ገቢ አለማድረጋቸው ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዳይኖር በማድረግ ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

**የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችት እና ስርጭት በቅንጅት መፈጸሙን በተመለከተ፡-**

97. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብዓት አቅርቦት፣ ክመችት እና ሥርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አራቱ (በደሴ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች ከግብርና ጽ/ቤቶች እና የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት እንደማይሰራ፣ ከማዳበሪያዎች እና ፀረ-አረሞች ውጪ በሌሎች ግብዓቶች ላይ ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከንግድ ባንክ ጋር ከሲፒኦ ጋር በተያያዘ ቶሎ ወደ ድርጅቱ አካውንት የማዘዋወሩን ሥርዓት እንዲፋጠን በቅንጅት የማይሰራ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም አንድ አንዴ ድርጅቱ የዋጋ ለውጥ በሚያደርግበት ወቅት ባለህብቶቹ ያስገቡት ገንዘብ ወደ ድርጅቱ ሂሳብ ቁጥር ባለመተላለፉ በባለህብቶቹ ላይ ተጽኖ ስለሚያሳድር ከድርጅቱ እምነት እንዲያጡ አድርጓል፡፡

99. የግብርና ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ፣ የግብርና ሚኒስቴር በክልሎች የቅንጅት ክፍተቶች መኖራቸው ወቅታዊ አቅርቦት ላይ እንቅፋት ስለሚሆን መስተካከል እንዳለበት፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የሥራ ኃላፊዎች እንደገለጹት ሁሉም የሚያገለግሉት አርሶ አደሩን በመሆኑ የሚሰጡትን አገልግሎት በሰለጠነ ሁኔታ ለመስጠት መቀናጀቱ አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት ኃላፊዎች ደግሞ በአንዳንድ ቦታዎች ክፍተት ያለ ቢሆንም ለወደፊት የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

100. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብዓት አቅርቦት፣ ክምችት እና ሥርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ጋር በቅንጅት አለመስራቱ በክምችት መጋዘን ውስጥ ያሉ ከማዳበሪያና ምርጥ ዘር ውጭ ግብዓቶች አርሶ አደሮች ድረስ እንዳይተዋወቁ በማድረግ በክምችት መጋዘን ውስጥ ለብልሽት እንዲዳረጉ ያደርጋል፤ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከንግድ ባንክ ጋር ተቀናጅቶ አለመስራቱ በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለህብቶች በወቅቱ ግብዓቶችን እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የሚያጓጉዙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ፡-**

101. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪ መኪናዎችን ኢኮኖሚያዊ በሆነ እና ውጤት በሚያስገኙበት ሁኔታ ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ ከ2004- 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ አብዛኛው የድርጅቱ የጭነት ተሽከርካሪዎች በኪሳራ እንዲቀሳቀሱ ተደርገዋል፤ ይህም በ2005 ዓ.ም 15 ተሽከርካሪዎች ብር 1,770,341.96 እና በ2004 ዓ.ም ብር 1,855,825.22 ኪሳራ ያሳዩ መሆኑን ከከባድ መኪና የገቢና ወጪ የስራ ክንውን ሪፖርት ክለሳ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም መወገድ የሚገባቸው 12 ተሽከርካሪዎች እና 13 ተሳቢ በየካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲወገዱ የቀረቡ ቢሆንም እስከ 2006 ዓ.ም እንዳልተወገዱ ታውቋል፤ ከዚህ በተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ የደርሶ መልስ ጭነት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፤ እንዲሁም የድርጅቱን ተሽከርካሪዎች ላይ የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ ከሌሎች የልማት ድርጅት ተሽከርካሪዎች ጋር በማቀናጀት በግብዓት ማመላለስ የጨረታ ሂደት ውስጥ መሳተፍ አለመቻላቸውን በኦዲቱ በተደረገው ቃለመጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

103. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የትራንስፖርት ዳይሬክቶሬቱ በቅርብ የተቋቋመ በመሆኑ የሃገር ውስጥ የመጓጓዣ እስታንደርድ መመሪያ ለማውጣት ዝግጅት ላይ መሆኑን፣ የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ከአንዴም ሶስቴ ጨረታ እንደወጣ እና ለመግዛት የቀረበ አለመኖሩን፣ ኪሳራን በተመለከተ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች በተከታታይነት ያልሰሩ በመሆናቸው የእርጅና ተቀናሻቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

104. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪዎችን በኪሳራ ማንቀሳቀስ እና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑትን ተሽከርካሪዎች በማስወገድ ከነርሱ የሚገኘውን ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረግ ድርጅቱ ማግኘት የሚገባውን እንዲያጣ በማድረግ የድርጅቱን አቅም ያዳክማል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችት እና ሥርጭት አፈጻጸምን በተመለከተ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች እንዲሁም መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የታዩት ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

105. የግብርና ምርት ማሳደጊያ ድርጅት ሽያጭ እና ሥርጭት ማዕከላት (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) እና በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን)፣ መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ/ደጋጊና፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ጥራት ያላቸው የምርት ማሳደጊያዎች ወቅቱን ጠብቀው እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ የማይቀርቡ መሆኑ፣

106. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ በበደሌ ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ በሚገኙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች፣ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሁለት ዩኒየኞች (አምቦና በቾ)፣ 4 መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ እና ያያ ጀቦ) ፣ በአማራ ክልል በታዩ ሶስት ዩኒየኖች (መርከብ፣ፀሐይ እና ጎዛምን) እና 3 መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት አለመከናወኑ፣

107. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና በታዩት በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች ፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህበረት ሥራ ማህበራት አርሶ አደሮች፣ ኢንቬስተሮች፣ የእርሻ ልማቶች ወ.ዘ.ተ የሚፈልጉትን የምርት ማሳደጊያዎች መጠን እና አይነት ሙሉ በሙሉ የማይጠየቁ እና በመረጃም ተጠናቅሮ አለመያዙ፣

108. ከላይ በተጠቀሱት እና በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ከክብደት በታች (Under Weight) 50 ኪ.ግ. መሆን ሲገባቸው የማዳበሪያቸው ከረጢት ሳይፈታ ከ44- 49 ኪ.ግ. የሆኑ የምርት ማሳደጊያዎች ለአርሶ አደሮች የሚደርሱዋቸው መሆኑ እንዲሁም በመጋዘን ውስጥ ለሚከሰቱ የግብዓቶች ፍሳሽ (ጉድለት) መጠን በየአመቱ ተጠናቅሮ በመረጃነት አለመያዙ፣

109. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ደርጅት በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ ቅርንጫፎች በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ውሳኔ የተሰጠበት ግብአት በተመላሽ የግበአት መረከቢያ ሰነድ (Stock Return Memo) ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እንዲሁም በአማራ ክልል በሚገኙ ጸሃይ ዩኒየን ፣ መርከብ ዩኒየን እና ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ መሰረታዊ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ቢደረግም የማቀያየር ሥራ እንጂ ተመዝግቦ የሚያዝ አለመሆኑ፣ በድርጅቱ ሥር የሚገኙ የነቀምት እና ባህር ዳር ያሉ ማዕከላዊ መጋዘኖች በስራቸው የሚተዳደሩትን የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላትን የክምችት መጠን በየጊዜው የሚቆጣጠሩበትን ዘዴ ዘርግተው ተግባራዊ አለማድረጋቸው፣

110. ናሙና በታዩት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ቅርንጫፎች (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) በቅጽ 4 ገቢ የተደረገበት፣ ከቅጽ 2(የታዘዘበት)፣ ከቅጽ 5(ወጪ) ፣ ከቅጽ 19 (ማርኬቲንግ ጣቢያዎች የሚረከቡበት ሰነድ) እንዲሁም ከቅጽ 3 (ለደንበኛ የሚሰጥ) ጋር ተነጻጽሮ የሚቀመጥበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት አለመኖሩን እና ከላይ በተገለጹት እና በናሙና በታዩት መጋዘኖች ውስጥ የማዳበሪያውን ዓይነት፣ የገባበትን ቀንና በድርድር ውስጥ የሚገኘው የማዳበሪያ መጠን፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ መለያ ካርድ(Bin Card) በድርድሩ ላይ አለመኖሩን፣

111. ከላይ በተጠቀሱትና በናሙና ተመርጠው በታዩት መጋዘኖች ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች በመጋዘኖቹ ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ አለመሆኑን እንዲሁም በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰቡ ግብዓቶች በተለየ ሥፍራ የማይቀመጡ መሆኑን እና ግብዓቶቹ በሚወጡበት ወቅት አወጣጡ በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ የገባው ቀድሞ እንዲወጣ አለመደረጉ፣

112. ከላይ በተጠቀሱት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት መጋዘኖች ከግብርና ግብአቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንብረቶች(ማዳበሪያ ከረጢቶች፣ ጀሪካን፣ ካርቶኖች፣ በርሜሎች፣ ማገዶዎች፣ ቆርቆሮዎች፣ ሌሎች ግብዓቶች ተቀላቅለው(ብረት ነክ እና ማዳበሪያዎች)…) በክምችት መጋዘን ውስጥ ተጣበው እንደሚቀመጡ መደረጋቸው፣

113. ከላይ በተጠቀሱና በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ መጋዘኖች ውስጥ አገልግሎት ላይ መዋል የሚገባቸው የመገልገያ መሳሪያዎች( አካፋና ዶማ ፣ ሴንጢ ፣መሰላል፣ የናሙና መያዣ ከረጢት፣ የኬሚካል ቱታ፣ ጎግል፣ ማስክ…) አለመሟላታቸው እና ከላይ በተጠቀሱት አከባቢዎች በሚገኙ

ዩኒየኖች እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የመጋዘን ሕንጻ አሰራር ጥራቱ የጠበቀ ሆኖ በየጊዜውም ክትትል ተደርጎ ተገቢው ጥገናም የማይደረግላቸው መሆኑ፣

114. በተራ ቁጥር 105 በተጠቀሱት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ መጋዘኖች የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚው ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብዓቶች ዝርዝር ተጠናቅሮ የማይያዝ እና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው አለመደረጋቸው አለመደረገቸው፣

115. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ደርጅት በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ሥር በሚገኙ ማከፋፈያ መጋዘኞች ሥለተደረገው ሽያጭ በማጠቃለል የሽያጭና የሥርጭት ማዕከሉ በየሳምንቱ ለዋናው መ/ቤት ለሽያጭና ሥርጭት ቡድን ሪፖርት እናደርጋለን ቢሉም የተጠናቀረ ሪፖርት አለመገኘቱን እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩ እና ከላይ በተገለጹት ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሳይሆን ሽያጭ በብዛት በሚከናወንበት ወቅት የተሸጠውን መጠን ብቻ የሚያሰውቁ መሆኑን እንጂ ቀጣይነት ባለው መልኩ በወር፣ በሩብ፣ በግማሽ አመት እና በአመት ሪፖርት አለመዘጋጀታቸው፣

116. በናሙና በታዩት እና ከላይ በተጠቀሱት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት፣ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የያዘ የሥርጭት ፕሮግራም እንደማያዘጋጁ እና መረጃዎቹንም አጠናቅረው የማይዙ መሆኑ፣ እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በሀገር ውስጥ ለሚደረገው የከባድ መኪና ተሸከርካሪዎች ጉዞ ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጃል ተብሎ የተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መመዘኛ (standard) ተዘጋጅቶ ተሸከርካሪው መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩን ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

117. ከላይ በተጠቀሱት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና የህብረት ሥራ ማህበራት ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ የሚለዩበት ሁኔታ ይኖራል ቢሉም የምርት ማሳደጊያዎቹ ዓይነት ዝርዝር እና የሚፈለጉበት ቦታ በመረጃነት ተጠናቅሮ አለመያዙ፣

118. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ፣ በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የግብዓቶች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት በሚገኙ የምርት ማሳደጊያዎች ላይ የማስተዋወቅ ሥራ የማይሰራ መሆኑ፣ በግብዓት ማከማቻ መጋዘን ለሚሰሩ ሰራተኞች የምርት ማሳደጊያዎች አያያዝ እና አጠቃቀም ሁኔታን በተመለከተ ሥልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ማስታወቂያዎች የሌሉ ሲሆን በተቀሩት ግን የቆዩ እና በደንብ የማይታዩ እና የማይነበቡ መሆናቸው፣

119. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በየጊዜው ልዩ ልዩ የሽያጭ ሥልቶችን በመንደፍ የሽያጭ መጠኑ እንዲጨምር እና የድርጅቱ ትርፋማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ የሽያጭ አውታሮችን ያልዘረጋና በየጊዜው እንዲሻሻሉ አለማድረጉ፣

120. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በድርጅቱ የክሬዲት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማድረጉ እና በአማራ ክልል ለአርሶ አደሮች የተሰጠ የግብዓቶች ብድር ወቅቱን ጠብቆ እንዲመልሱ አለመደረጉ፣

121. በናሙና ተመርጠው በታዩት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና የህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ… ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) አለመዘጋጀቱ እና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የተጠያቂነት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

122. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና በታዩት አራቱ( በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች ያሉት ግብዓቶች ውስን መሆናቸው ይህም የላብራቶሪ እቃዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች የተለያዩ የጓሮ አተክልቶች፣ የእንስሳት መደሃኒቶች፣ የአበባ ማዳበሪያዎች … በጣቢያዎቹ አለመኖሩን እና ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑ፣

123. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ሲከናወን በዕለቱ ባንክ ገቢ እናደርጋለን ቢሉም በየቀኑ የተሰበሰበት መረጃ ባንክ ከገባበት(slip) ጋር ተነጻጽሮ መቅረብ አለመቻሉ እንዲሁም በዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ሲከናወን የተሰበሰበው ገንዘብ እስከ አንድ ወር ድረስ በአርሶ አደሩ እጅ የሚቆይ መሆኑ፣

124. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ጣቢያዎች ከግብርና ጽ/ቤቶች እና የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት አለመሰራቱ፣ ከማዳበሪያዎች እና ፀረ-አረሞች ውጪ በሌሎች ግብዓቶች ላይ ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከንግድ ባንክ ጋር ከሲፒኦ ጋር በተያያዘ ቶሎ ወደ ድርጅቱ አካውንት የማዘዋወሩን ሥርዓት እንዲፋጠን በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣

125. ከ2004- 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ አብዛኛው የጭነት ተሽከርካሪዎች በኪሳራ እንዲቀሳቀሱ መደረጋቸው፤ እንዲሁም መወገድ የሚገባቸው 12 ተሽከርካሪዎች እና 13 ተሳቢ በየካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲወገዱ የቀረቡ ቢሆንም እስከ አሁን 2006 ዓ.ም እንዲወገዱ አለመደረጋቸው ፣ ተሽከርካሪዎችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ የደርሶ መልስ ጭነት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

126. በአጠቃላይ የግብርና ሚኒስቴር፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችት እና ሥርጭት አፈጻጸም ላይ በቅንጅት አለመሰራቱ ከላይ የተጠቀሱት ግኝቶች እንዲፈጠሩ አስችሏል፡፡ ስለሆነም በቅንጅት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን በወቅቱ ፣በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሮች እንዲቀርብ አለመደረጉ ሀገሪቷ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ወደ ኢንደስትሪው መር ለመምጣት ያቀደችውን ግብ በተሟላ መልኩ እንዳይሳካ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ግድፈቶች በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችት እና ሥርጭት ሥርዓትን ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

127. የሀገራችን 85% አርሶ አደሩ እንደ መሆኑ መጠን የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ከፍ እንዲል ለማድረግ ጥራት ያላቸው የምርት ማሳደጊያዎች ወቅቱን ጠብቀው እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ ሊቀርቡ ይገባል፡፡

128. የምርት ማሳደጊያዎችን ለአርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ እንዲቻል የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት ሊያከናውኑ ይገባል፡፡

129. የግብርና ማሳደጊያዎች መጋዘን እንዳይጣበብ እና ግብዓቶቹም በየአመቱ እየከረሙ ለብልሽት እንዳይዳረጉ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሚከናወነው ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

130. አርሶ አደሮች በድርጅቱ እና በኤጀንሲው ላይ ያለው እምነት ጠንካራ ሆኖ እንዲቀጥል እና ለብልሹ አሰራር በር እንዳይከፈት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ከክብደት በታች (Under Weight) የግብርና ግብዓት ከወደብ እንዳይቋጠርና ወደ መሀል አገር እንዳይጓጓዝ በተለይም ተጠቃሚው ወደ ሆነው አርሶ አደር በቀጥታ እንዳይደርስ እንዲሁም ሾፌሩ ጭነት በጫነበትና ዕቃውን ወይም ጭነቱን ባስረከበበት ሰነዶች መካከል የባከነ ንብረት ወይም ልዩነት እንዳይኖር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባቸዋል፡፡

131. የቁጥጥር ፣ ክትትል እና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲጠናከር የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ውሳኔ የተሰጠበትን ግብአት በተመላሽ የግበአት መረከቢያ ሰነድ (Stock Return Memo) ገቢ በማድረግ፣ ማዕከላዊ መጋዘኖችን የሚያስተዳድሩ የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት የክምችት መጠን አመልካቾችን (Inventory Control Indicators) ለተመረጡ ግብርና ግብአቶች በመጠቀም ክምችታቸውን እየገመገሙ የአቅርቦት ጥያቄያቸውን ለግብርና ግብአት ግብይት የሥራ ሂደት ሊያቀርቡ፤ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘኖች የማዳበሪያውን ዓይነት፣ የገባበትን ቀንና በድርድር ውስጥ የሚገኘው የማዳበሪያ መጠን፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ መለያ ካርድ(Bin Card) በድርድሩ ላይ በቀላሉ ለማየት በሚቻልበት ሁኔታ ሊንጠለጠል እና የገቢ፣የወጪ እና የሽያጭ መረጃዎችን ተጠናቅረው ሊይዙ ይገባል፡፡

132. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች በመጋዘን ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ፣ በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰበ ግብዓት በተለየ ሥፍራ ፣ ሳይበላሹ እና ሳይጎዱ

የሚቀመጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም በሚወጡበት ወቅት አወጣጡ በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ የገባው ቀድሞ ሊወጣ ይገባል፡፡

133. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን ጥራታቸው ሳይጓደል ለማስቀመጥ እና ትክክለኛውን ግብዓት ለአርሶ አደሮች ለማድረስ ይቻል ዘንድ የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘኖች ሕንጻ አሰራር ጥራታቸውን የጠበቁ ሆነው በየጊዜውም ክትትል ተደርጎ ተገቢው ጥገና ሊደረግላቸው እና በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የመገልገያ መሳሪያዎችም በመጋዘኖቹ ውስጥ ተሟልተው ሊገኙ እንዲሁም የምርት ማሳደጊያዎች አያያዝ ሁኔታ በሚመለከተው ኃላፊ በየጊዜው ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

134. የምርት ማሳደጊያዎች ለብክነት እንዳይጋለጡ እንዲሁም ጥራታቸው ሳይጓደል ወደ ተጠቃሚው እንዲደርሱ በማንኛውም ምክንያት በማዕከል እና በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት መጋዘኖች የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚ ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብአቶች ዝርዝር ሊያዝ ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው እንዲሁም በዕቅድ የተገዙ ግብዓቶች ለብክነት ሳይጋለጡ ሊሸጡ እና በሽያጭ ረገድ የደረሱ ምዝበራና ብክነትን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድባችው ይገባል፡፡

135. የቁጥጥር፣ ክትትል እና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ በወር፣ በሩብ ፣ በግማሽ አመትና በአመት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ግብዓቱ አይነት በቀን ወይም በሳምንት ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡

136. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች በየአመቱ ከፍላጎት በላይ እየሆኑ ለብልሽት እንዳይዳረጉ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በተዘጋጀውም የሥርጭት ፕሮግራም መሠረትና ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ በመመርኮዝ የግብርና ግብዓት ሥርጭት ሊፈጸም፣ የሚያጓጉዝበትን የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የጣቢያዎችን ዝርዝር የያዘ የስርጭት ፕሮግራም ተጠናቅሮ ሊያዝ እና ሥምሪት የወሰደው ሾፌርም በተሰጠው ስምሪት መሰረት ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጃል ተብሎ በተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መሰረት መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

137. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች በመሸጋሸግ ሂደት ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳረጉ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት

አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ መለየት አለበት፡፡

138. የአቅራቢዎቹ አቅም እንዲያድግ እና ተጠቃሚዎች ስለምርት ማሳደጊያዎቹ አጠቃቀም እና አያያዝ አውቀው እንዲገዙት የምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት የሚገኙ ግብዓቶች ወደ ደንበኛው ቀርበው ሊተዋወቁ፣ በምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭት እና ክምችት ዙሪያ ለተሰማሩ ሠራተኞች ሙያቸውን ለማሻሻል እንዲችሉ ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው፣ ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ያሉበትን ሥፍራ ሊጠቁሙ የሚችሉ ማስታወቂያዎች ሊኖሩ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ኢኮኖሚያዊ የማከፋፈያና የሽያጭ አውታሮችን ሊዘርጋና በየጊዜው እንዲሻሻሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

139. ተጠቃሚዎች ከክሬዲት ፖሊሲው ተጠቀሚ እንዲሆኑ እና አቅራቢዎችም የሚሸጡት ግብዓቶች መጠን እንዲጨምር የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ የተፈቀደውን የክሬዲት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በአመት ውስጥ በዱቤ ሊሸጥ የታቀደው የግብዓት ዋጋን ሊተመኑና ለመሰብሰብም ፕሮግራም ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡

140. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዙሪያ ያሉ ራተኞችን የሥራ ፍላጎት ለመገንባት እና የስራ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ለማድረግ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ... ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) ሊያዘጋጅና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የቅጣት አሠራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

141. የአርሶ አደሮችን ምርት እና ምርታማነትን ለማሻሻል እንዲሁም እንዲጨምር ለማድረግ ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች ትኩረት ሊሰጥ እንዲሁም ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡

142. ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር እንዲሁም የአቅራቢዎቹ ገንዘብ ለብክነት እንዳይጋለጥ በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ በተከሄደበት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ባንክ ካለ በዕለቱ እና ባንክ ከሌለ ሠራተኛው የሰበሰበውን ጥሬ ገንዘብ በካዝና በማስቀመጥ በሶስት ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ባንክ በመሄድ ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

143. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ግብዓቶች ሙሉ በሙሉ ለአርሶ አደሩ ለማስተዋወቅ እና ግብዓቶቹን በወቅቱ ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ለማድረግ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብዓት አቅርቦት፣ ክመችት እና ሥርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

144. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የተቋቋበትን አላማ ለማሳካት እና አቅሙን ለማጎልበት ተሽከርካሪ መኪናዎችን ኢኮኖሚያዊ በሆነ እና ውጤት በሚያስገኙበት ሁኔታ ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡

በመጨረሻም የግብርና ሚ/ር፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ፣የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ እንዲሁም በኦዲቱ በታዩ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን በሙሉ በማቅረብ እና ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ- 1

**<u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>**

| **የኦዲት ጭብጥ**<br><br>(Audit Issues) | **የመገምገሚያ መስፈርት**<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1.የግብርና ምርት ማሳደጊዎች | 1. ድርጅቱ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ ከማከናወኑ በፊት የግዥ ዓቅድ ማዘጋጀት አለበት፡፡ |

| | |
|---|---|
| አቅራቢ ድርጅት የምርት ማሳደጊያዎችን በወቅቱ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚያስችል የግዥ ሥርዓት መዘርጋቱን ማጣራት፤ | 2. ድርጅቱ የሚፈለገውን የግብርና ግብዓት በጥራት፣ በወቅቱና በዝቅተኛ ዋጋ እንዲቀርብ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 3. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 4. ዓመታዊ የድርጅቱ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ |
| | 5. ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች፣ ግብዓቶቹ መጋዘን መድረሳቸው ሲረጋገጥ ብቻ ለአቅራቢው ቀሪው 10% ክፍያ እንዲለቀቅ ለባንክ የክፍያ ትዕዛዝ መሰጠት አለበት፡፡ |
| | 6. የግብርና ግብዓቶቹ ወደብ ወይም ኤርፖርት ከመድረሳቸው በፊት ለጉምሩክ ለወደብ ፎርማሊቲ ማጠናቀቂያ የሚያስፈልጉ ሰነዶች (ኤር ዌይቢል፣ የባንክ ዴሊቨሪ ኦርደር፣ ቢል ኦፍ ሎዲንግ፣ ቻንበራይዝድ ኢንቮይስ፣ ፓኪንግ ሊስት…) ሊሟሉ ይገባል፡፡ |
| | 7. ለጓሮ አተክልት ዘር ወይም ለኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ ከግብርና ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት እንዲያመች ከገቢ ዕቃዎቹ ከየዓይነታቸው ናሙናዎች እንዲላኩ መደረግ አለባቸው፡፡ |
| | 8. በሰነድ ላይ ከተመለከተው የመጠንና የዓይነት ለውጥ እንዲሁም በብልሽት የታዩ ልዩነቶችን በገቢ ሰነድ ላይ እንዲሰፍሩ ማድረግና የካሣ ጥያቄ ለመድን ለማቅረብ እንዲቻል ወዲያውኑ ለግብርና ግብዓት ግብይት የሥራ ሂደት በጽሁፍ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡ |
| | 9. ከክብደት በታች (Under Weight) የግብርና ግብዓት ከወደብ እንዳይቋጠርና ወደ መሀል አገር እንዳይጓጓዝ በተለይም ተጠቃሚው ወደ ሆነው አርሶ አደር በቀጥታ እንዳይደርስ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡ |
| | 10. በቢል ኦፍ ሎዲነግና ኢንስፔክሽን ሪፖርቱ መካከል ለሚታየው ጉድለት መድን ድርጅት/ አቅራቢው ድርጅት/ ከመጨረሻው 10% ክፍያ ላይ በውሉ መሰረት እንዲቀንስ ሊደረግ እና እንዲሁም በማሪታይም ዌይቢልና በቅጽ 4 መካከል ለሚታየው |

| | |
|---|---|
| | ጉድለት ከአጓጓዥ ድርጅት የትራንስፖርት ሂሳብ በውሉ መሠረት መቀነስ አለበት፡፡ |
| 2. የምርት ግብዓት ማሳደጊያዎች ክምችትን ደህንነት ለማስጠበቅና የተቀላጠፈ አሠራር እንዲኖር ለማድረግ ለግብዓቶች በቂ፣ አስተማማኝ እና በሥርዓት የተደራጁ ማከማቻ መጋዘኖች መዘጋጀታቸውን ማጣራት፤ | 11. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች ሳይበላሹና ሳይጎዱ የሚቀመጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. የመጋዘኑ ሕንጻ አሰራር ጥራቱን የጠበቀ ሆኖ በየጊዜውም ክትትል ተደርጎ ተገቢው ጥገና የተደረገለት መሆን አለበት፡፡ |
| | 13. በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የመገልገያ መሳሪያዎች በመጋዘን ውስጥ ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ |
| | 14. የማዳበሪያውን ዓይነት፣ የገባበትን ቀንና በድርድር ውስጥ የሚገኘው የማዳበሪያ መጠን፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ መለያ ካርድ(Bin Card) በድርድሩ ላይ በቀላሉ ለማየት በሚቻልበት ሁኔታ መንጠልጠል ይኖርበታል፡፡ |
| | 15. የማዳበሪያ አያያዝ ሁኔታ በሚመለከተው ኃላፊ በየጊዜው ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡ |
| | 16. የግብርና ግብዓቶች በመጋዘን ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ |
| | 17. የግብርና ግብአቶች በሚወጡበት ወቅት አወጣጡ በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ ከገባው ወደ ኋላው ማንሳት እንጂ ኋላ ከገባው መሆን የለበትም፡፡ |
| | 18. በጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኞች እንዲሰበሰብ ውሳኔ የተሰጠበት ግብአት በተመላሽ የግበአት መረከቢያ ሰነድ (Stock Return Memo) ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 19. በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰበ ግብዓት በተለየ ሥፍራ መቀመጥ እና ተገቢው እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡ |
| | 20. በማንኛውም ምክንያት በማዕከል እና በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት መጋዘኖች የሚወገዱ ግብአቶች ዝርዝር በየ3 ወሩ ለዋናው መ/ቤት ለግብርና ግብዓት ግብይት እና ለኮርፖሬት ፕላንና ፋይናንስ የሥራሂደቶች ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡ |
| | 21. ለተጠቃሚ ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብአቶች ዝርዝር ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡ |
| | 22. ማዕከላዊ መጋዘኖችን የሚያስተዳድሩ የሽያጭና |

| | |
|---|---|
| | ሥርጭት ማዕከላት የክምችት መጠን አመልካቾችን (Inventory Control Indicators) ለተመረጡ ግብርና ግብአቶች በመጠቀም ክምችታቸውን እየገመገሙ የአቅርቦት ጥያቄያቸውን ለግብርና ግብአት ግብይት የሥራ ሂደት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 23. ከግብርና ግብአቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንብረቶች በክምችት መጋዘን እንዳያጣብቡ በወቅቱ መሸጥ አለባቸው፡፡ |
| 3. የምርት ማሳደጊያዎች ሥርጭት ሥርዓት የተጠቃሚው ፍላጎት እና አቅም መሠረት ያደረገና ግብዓቶቹም በወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲጓጓዙ መደረጉንና በትክክል መድረሳቸውን እንዲሁም መሸጣቸውን ማጣራት፤ | 24. በመርከብ ተጭኖ የመጣው የግብርና ግብዓት መጠን ወደ መሐል አገር ተሰራጭቶ እንዳለቀ በትክክል በማዕከላዊ ማከፋፈያ መጋዘን/በየጣቢያው ለመድረሱ ማረጋገጫ በተዘጋጀው ሪከርድ መያዝ አለበት፡፡ |
| | 25. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብዓት ኦፕሬሽን ሥራ እንደተጠናቀቀ በአስተላላፊነት ከተመረጠው ድርጅት የማጠቃለያ የሥርጭት ሪፖርት /Final Dispatch Report/ ተዘጋጅቶ እንዲላክ ጥያቄ በማቅረብ ተከታትሎ ሊያስፈጽም ይገባል፡፡ |
| | 26. የግብርና ግብአቶች ወደብ /ኤርፖርት ከመድረሳቸው በፊት ወይም በአገር ውስጥ በክምችት ያሉ የግብርና ግብዓቶች ወደ ሌሎች ቦታዎች ከመሰራጨታቸው በፊት የሥርጭት ፕሮግራም ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡ |
| | 27. በተዘጋጀው የሥርጭት ፕሮግራም መሠረትና ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ በመመርኮዝ የግብርና ግብዓት ሥርጭት ሊፈጸም ይገባል፡፡ |
| | 28. በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ሥር የሚገኙት ማዕከላዊ ማከፋፈያ መጋዘኖች ወይም ማርኬቲንግ ጣቢያዎች ከወደብ የደረሱአቸውን የግብርና ግብአቶች በመጋዘን ሰራተኞች አማካይነት በቅጽ 4 ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 29. ማዕከላዊ ማከፋፈያዎችን የሚያስተዳድሩ የሽያጭ ስርጭት ማዕከላት ከሥራ ሂደቱ በሚሰጣቸው የሥርጭት ትዕዛዝ መሠረት በቅጽ 5 ወጪ በማድረግ ወደሚመለከታቸው መጋዘኖች/ማርኬቲንግ ጣቢያዎች ሊልኩ ይገባል፡፡ |
| | 30. ማርኬቲንግ ጣቢያዎችም በቅጽ 5 የተላከውን የግብርና ግብዓት በቅጽ 19 ሰነድ ተረክበው ገቢ ካደረጉ በኋላ ስለተረከቡት ግብዓት ዓይነትና መጠን |

| | |
|---|---|
| | ዝርዝር ሪፖርት ለሚያስተዳድራቸውና ግብአቱን ለላከላቸው ሽያጭና ስርጭት ማዕከላት ሊያስተላልፉ ይገባል፡፡ |
| | 31. ከማርኬቲንግ ጣቢያ ወደ ማርኬቲንግ ጣቢያ የግብርና ግብዓት ሽግሽግ ማድረጉ ከገበያ ጠቀሜታ አንጻር ሲታመንበትና ከጣቢያዎቹ ፍጆታ በላይ የሆነ እንዲሁም የማይሸጥ የግብርና ግበአት ሲኖር ከሽያጭና ሥርጭት ማዕከሉ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፡፡ |
| | 32. ድርጅቱ የምርት ግብዓቶችን ከማዕከላዊ ማከፋፈያ መጋዘኖች ወደ ማርኬቲንግ ጣቢያዎች የሚያጓጉዝበትን የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የጣቢያዎችን ዝርዝር የያዘ የስርጭት ፕሮግራም አጠናቅሮ መያዝ ይኖርበታል፡፡ |
| | 33. ሥምሪት የወሰደ ሾፌር በተሰጠው ስምሪት መሰረት ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጃል ተብሎ በተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መሰረት መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 34. ሾፌሩ ጭነት በጫነበትና ዕቃውን ወይም ጭነቱን ባስረከበበት ሰነዶች መካከል የባከነ ንብረት ወይም ልዩነት ሥለ መኖሩ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡ |
| | 35. የግብዓቶች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት የሚገኙ ግብዓቶችን ወደ ደንበኛው ቀርበው ሊተዋወቁ ይገባል፡፡ |
| | 36. በዕቅድ የተገዙ ግብዓቶች ለብክነት ሳይጋለጡ መሸጥ አለባቸው፡፡ |
| | 37. በሽያጭ ረገድ የደረሱ ምዝበራና ብክነትን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 38. የሽያጭ ዋጋን በትክክል ለመተመን አስፈላጊው ዝግጅትና ተሳትፎ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 39. ድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ የማከፋፈያና የሽያጭ አውታሮችን መዘርጋትና በየጊዜው እንዲሻሻል ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 40. በድርጅቱ ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ መለየት አለበት፡፡ |
| | 41. በወር፣ በሩብ ፣ በግማሽ አመትና በአመት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ግብዓቱ አይነት በቀን ወይም በሳምንት ሊሸጥ የታቀደው |

| | |
|---|---|
| | ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ መዘጋጀት አለበት፡፡ |
| | 42. የተፈቀደውን የክሬዲት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በአመት ውስጥ በዱቤ ሊሸጥ የታቀደው የግብዓት ዋጋ ሊተመንና ለመሰብሰብም ፕሮግራም ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 43. በሽያጭ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ሠራተኞች ሙያቸውን ለማሻሻል እንዲቻል ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 44. በድርጅቱ ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ… ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) ሊያዘጋጅና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የቅጣት አሠራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 45. በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ሥር በሚገኙ ማከፋፈያ መጋዘኖች ሥለተደረገው ሽያጭ በማጠቃለል የሽያጭና የሥርጭት ማዕከሉ በየሳምንቱ ለዋናው መ/ቤት ለሽያጭና ሥርጭት ቡድን ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 46. ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ከተሰጣቸው የሥልጣን ውክልና በላይ የሚቀርብ የግዥ ጥያቄ እንደሥልጣን ውክልና ደረጀው ለዋና ዳይሬክተር ወይም ለግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክተር በማሳወቅ ሲፈቀድ ብቻ ሽያጭ ሊፈጸም ይገባል፡፡ |
| | 47. በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ በተከሄደበት ጣቢያ ባንክ ካለ በዕለቱ እና ባንክ ከሌለ ሠራተኛው የሰበሰበውን ጥሬ ገንዘብ በካዝና በማስቀመጥ በሶስት ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ባንክ በመሄድ የድርጅቱ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 48. የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ያሉበትን ሥፍራ ሊጠቁሙ የሚችሉ ማስታወቂያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ |
| | 49. ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች ትኩረት ሊሰጥ እንዲሁም ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡ |
| | 50. ድርጅቱ የግብርና ግብዓት ሥርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 51. ድርጅቱ በየጊዜው ልዩ ልዩ የሽያጭ ሥልቶችን በመንደፍ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 52. ማዳበሪያ በሚጓጓዝበት ወቅት ከረጢት ሲቀደድና ከወደብ ሲመጣ ከ50 ኪ.ግ በታች ከሆነ በአዲስ በመቀየር በየደረጃው በሚቋቋመው የሪባግ ኮሚቴ አማካይነት ማዳበሪያውን ሪባግ በማድረግ ክብደቱ እንዲስተካከል መደረግ አለበት፡፡ |

አባሪ- 2

በኦሮሚያ ክልል መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ሥር የሚገኙ አርሶ አደሮች ጥያቄ እና መልሳቸው የተጠናቀረ፤

| መለኪያ የአርሶ አደር ብዛት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | መስፈርት | ነቀምት ያያ ጀቦ ገ/ማህበር | | አምቦ ሙቱሉ ገ/ማህበር | | ወሊሶ ደጋጊና ገ/ማህበር | | ወሊሶ አዋሽ ቡኔ ገ/ማህበር | | ድምር | |
| | | አዎ | አይደለም | አዎ | አደለም | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም |
| 1. | ግብዓቶች ወቅቱን ጠብቀው ይቀርባሉ? | 2 | 8 | 5 | 1 | 7 | 3 | 8 | 3 | 22 | 15 |
| 2. | ስለ ግብርና ግብዓቶች አጠቃቀም ትምህርት ይሰጣል? | 9 | 1 | 2 | 4 | 2 | 8 | 4 | 7 | 17 | 20 |
| 3. | ያልተጭበረበሩና ትክክለኛ ግብዓቶችን ለይተው ያውቃሉ? | 4 | 6 | 1 | 5 | 2 | 8 | 3 | 8 | 10 | 27 |
| 4. | በግብዓቶች ሽያጭ ወቅት የሚደረገው መስተንግዶ ጥሩ ነው? | 8 | 2 | 6 | 0 | 9 | 1 | 11 | 0 | 34 | 3 |
| 5. | የግብዓቶች አጠቃቀማችሁ እየጨመረ ነው? | 5 | 5 | 6 | 0 | 6 | 4 | 8 | 3 | 25 | 12 |
| 6. | ግብ ዓቶችን አርሶ አደሩ በተሰጠው ሙያዊ ምክር መሰረት ይጠቀማል? | 3 | 7 | 3 | 3 | 4 | 6 | 2 | 9 | 12 | 25 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7. | የጥራት ወይም የክብደት ማነስ ችግር ያለባቸው ግብዓቶች አጋጥሞታል? | 9 | 1 | 3 | 3 | 7 | 3 | 8 | 3 | 27 | 10 |
| 8. | በግብዓቶች ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ አካላት አጋጥሞታል? | 4 | 6 | 0 | 6 | 3 | 7 | 2 | 9 | 9 | 28 |
| 9. | ግብዓቶችን ነጋዴዎች ከመሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ሲገዙ አይተው ያውቃሉ? | 0 | 10 | 3 | 3 | 3 | 7 | 1 | 10 | 7 | 30 |
| 10. | ግብዓቶችን በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ይጠቀማሉ? | 4 | 6 | 2 | 4 | 5 | 5 | 8 | 3 | 19 | 18 |
| 11. | በአመት ውስጥ ሰለሚፈልጉዋቸው ግብዓቶች ቀደም ብለው ተጠይቀው ያውቃሉ? | 5 | 5 | 5 | 1 | 3 | 7 | 7 | 4 | 20 | 17 |
| 12. | በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ድርጅት የሚቀርበው ዋጋ ከሌሎች ሲነጻጸር ይቀንሳል? | 4 | 6 | 6 | 0 | 4 | 6 | 6 | 5 | 20 | 17 |

በአማራ ክልል መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ሥር የሚገኙ አርሶ አደሮች ጥያቄ እና መልሳቸው የተጠናቀረ፤

| ተ.ቁ. | መስፈርት | መለኪያ የአርሶ አደር ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ባህርዳር ምሥራቅ ጮራ ገ/ማህበር | | በባህርዳር መርዓዊ ገ/ማህበር | | ደብረማርቆስ ወንቃ ገ/ማህበር | | ድምር | |
| | | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም |
| 1 | ግብዓቶች ወቅቱን ጠብቀው ይቀርባሉ | 1 | 9 | 4 | 6 | 10 | 2 | 15 | 17 |
| 2 | ስለ ግብርና ግብዓቶች አጠቃቀም ትምህርት ይሰጣል | 4 | 6 | 7 | 3 | 9 | 3 | 20 | 12 |
| 3 | ያልተጭበረበሩና ትክክለኛ ግብዓቶች ለይተው ያውቃሉ | 5 | 5 | 6 | 4 | 7 | 5 | 18 | 14 |
| 4 | በግብዓቶች ሽያጭ ወቅት የሚደረገው መስተንግዶ ጥሩ ነው | 9 | 1 | 8 | 2 | 9 | 3 | 26 | 6 |
| 5 | የግብዓቶች አጠቃቀማችሁ እየጨመረ ነው | 5 | 5 | 6 | 4 | 9 | 3 | 20 | 12 |
| 6 | ግብዓቶችን አርሶ አደሩ በተሰጠው ሙያዊ ምክር መሠረት ይጠቀማል | 3 | 7 | 7 | 3 | 6 | 6 | 16 | 16 |
| 7 | የጥራት ወይም የክብደት ማነስ ችግር ያለባቸው ግብዓቶች አጋጥሞዎታል | 8 | 2 | 8 | 2 | 7 | 5 | 23 | 9 |
| 8 | በግብዓቶች ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ አካል አጋጥሞታል | 2 | 8 | 6 | 4 | 6 | 6 | 18 | 18 |
| 9 | ግብዓቶችን ነጋዴዎች ከመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ሲገዙ አይተው ያውቃሉ | 1 | 9 | 1 | 9 | 0 | 12 | 2 | 30 |
| 10 | ግብዓቶችን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይጠቀማሉ | 10 | 0 | 1 | 9 | 12 | 0 | 23 | 9 |
| 11 | በዓመት ውስጥ ስለሚፈለጉአቸው ግብዓቶችና ቀደም ብለው ተጠይቀው ያውቃሉ | 4 | 6 | 7 | 3 | 4 | 8 | 15 | 17 |
| 12 | በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሚቀርበው ዋጋ ከሌሎች ሲነፃፀር ይቀንሳል | 6 | 4 | 1 | 9 | 11 | 1 | 18 | 14 |